# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የቱሪዝም ፖሊሲ

# (የፀደቀ)

የካቲት/2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## ማውጫ

1. መግቢያ ..... 1
2. የፖሊሲው መነሻዎች ..... 2
3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ መርሆች እና ዓላማዎች ..... 3
4. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች ..... 6
4.1. የቱሪዝም መዳረሻ ልማት እና አስተዳደር ..... 6
4.2. የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ ቅርሶች ጥበቃ እና አጠቃቀም ..... 11
4.3. በቱሪዝም ዘርፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ..... 14
4.4 የግል ዘርፉ ተሳትፎ ..... 15
4.5 የአገልግሎት ጥራት ..... 18
4.6 የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ ..... 20
4.7 የቱሪዝም ዘርፍ አቅም ግንባታ ..... 23
4.8 ትብብር እና ስልታዊ አጋርነት ..... 25
5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች ..... 27
6. የቱሪዝም ፖሊሲ የማውጣት ስልጣን እና ወሰን ..... 28
7. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ..... 28
7.1 ፖሊሲውን የሚያስፈፅሙ ተቋማት እና ኃላፊነት ..... 28
7.2 የፖሊሲው ማስፈጸሚያ የሕግ ማዕቀፎች እና አሠራሮች ..... 33
7.3. የቱሪዝም ፖሊሲውን ቁልፍ ውጤቶች ለማረጋገጥ የሚከናወኑ የልማት ፕሮግራሞች ..... 33
7.4 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈፃፀም የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ..... 35
8. ሌሎች ተዛማጅ የልማት ፖሊሲዎች ..... 36
9. መሰረታዊ የቃላት ፍቺ ..... 37

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ዓይነተ-ብዙ እና መጠነ-ሰፊ የቱሪዝም ፀጋዎች ያሏት አገር ናት፡፡ እነዚህ ድንቅ የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ሃብቶች አገራችን በቱሪዝም ዘርፍ ሰፊ የልማት እድል እንድትጎናፀፍ አስችለዋታል፡፡ የቱሪዝም ዘርፍ ያሉንን መስህቦች በማልማትና መዳረሻዎችን በማስፋፋት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ እድገት እና መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ጉልህ ድርሻ እንዳለው ይታወቃል፡፡ ዘርፉ የውጭ ምንዛሬ በማመንጨት፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ አገራዊ ገቢን በማሳደግ፣ በመዳረሻ አካባቢ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ በማድረግ፣ ቅርሶችን በመጠበቅ እና የአገርን ገጽታ በመገንባት ረገድ የራሱን አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡

የቱሪዝም ዘርፍ ለአገራችን የሚያበረክተውን ፈርጀ-ብዙ አስተዋጽኦ ለማሳደግ እንዲቻል የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡ ይህን ተከትሎ በተከታታይ ዓመታት ተግባራዊ በተደረጉ አገራዊ የልማት ስትራቴጂዎች እና የፖሊሲ አቅጣጫዎች መሰረት ዘርፉ ለፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ሰፊ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የጎብኝዎች ፍሰት እና ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ እንዲጨምር፣ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ እና የስራ እድሎች እንዲፈጠሩ የተደረገ ዘርፉ ለጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት (Gross Domestic Product - GDP) የሚያበረክተው ቀጥተኛ አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ ዓይደለም፡፡ በሌላ መልኩ አገራችን ባለፉት ዓመታት ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ የዘርፉን ማህበራዊ ፋይዳ ከማጉላት ባለፈ ድህነትን በመቅረፍ ረገድ የራሱን አዎንታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የቱሪዝም ሀብት አንፃር የተገኙ ውጤቶች አጥጋቢ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ አገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት የቱሪዝም ተወዳዳሪነት ደረጃ ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ነባሩ የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ ዘርፉ የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ከማስቻል አኳያ ውስንነቶች ነበሩበት፡፡ የተቀናጀ እና ቀጣይነት ያለው የቱሪዝም ልማትን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ አዳዲስ መዳረሻዎችን የማልማት ስራ አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም የመስህቦች ተደራሽነት በሚፈለገው ደረጃ አለመጠናከር ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም ውጤታማ የግብይት እና ማስተዋወቅ ሥራ በበቂ ሁኔታ ባለመከናወኑ አዳዲስ ገበያዎችን መፍጠር ብሎም የገበያ ድርሻን ትርጉም ባለው ደረጃ ማሳደግ አልተቻለም፡፡ ምቹ የንግድ ስነ-ምህዳር ባለመፈጠሩ አነስተኛ እና መካከለኛ የቱሪዝም ንግድ ተቋማትን በማስፋፋትና በዘርፉ የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ሰፊ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ በጥቅሉ ፖሊሲው ዘርፉን ተብትበው ያሰሩትን ቁልፍ ተግዳሮቶች ከመፍታት አንፃር ሲመዘን በርካታ ክፍተቶች የታዩበት ነው፡፡

ስለሆነም አገራችን ያላትን ሰፊ የቱሪዝም ሀብት መሰረት በማድረግ የቱሪዝም መዳረሻዎችን እና ምርቶችን በማስፋፋት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ይጠበቅብናል፡፡ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር፣ በዘርፉ የአገልግሎት ልህቀትን ማረጋገጥ፣ ከጎብኝ አመንጪ አገራት ጋር ጠንካራ የገበያ ትስስር በመፍጠር የጎብኝዎችን ፍሰት እና የገበያ ድርሻን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ሃብቶች ጥበቃ እንዲጠናከር እና ዘላቂ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ለማድረግ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለውን ትስስር ማጠናከር ወሳኝ ነው፡፡ ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ እንዲጨምር እና ለአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት እድገት የሚያበረክተውን ድርሻ በጉልህ ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ ነባሩን ፖሊሲ መከለስ

አስፈልጓል፡፡ ስለሆነም እንደ አገር ለቱሪዝም ዘርፍ የተሰጠውን ትኩረት እንደመልካም እድል በመጠቀም ያልተፈቱ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ፣ የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት፣ የዘርፉን የመልማት አቅም እና እድሎችን አሟጦ መጠቀም እንዲቻል ፖሊሲውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፋዊ የቱሪዝም ፍላጎቶች እና ለውጦች ጋር የሚከሰቱ ተለዋዋጭ ባህሪያት ጋር በተጣጣመ መልኩ ዘርፉን በመምራት የሚፈለገውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጥቅም እንዲያመነጭ ለማስቻል ነባሩ ፖሊሲ በጥልቀት እንዲከለስ ተደርጓል፡፡

## 2. የፖሊሲው መነሻዎች

በነባሩ የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ የአገራችንን የቱሪዝም ዘርፍ በሰፊ የልማት አቅጣጫ የመምራት እሳቤን የያዘ ሲሆን ነባር እና አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦችን እንዲሁም መዳረሻዎችን ለማልማት፣ ለቱሪዝም ልማት ወሳኝ የሆኑ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ለማስፋፋት እንዲሁም በዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት በማስተዋወቅና በግብይት ሥራዎች አማካኝነት ጠንካራ የገበያ ትስስር ለመፍጠር፣ በቱሪዝም ልማት ውስጥ በሚሳተፉ ተዋንያን መካከል ትብብራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር እና በዘርፉ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የሚታየውን የአቅም ውስንነት ለመቅረፍ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች እና ስትራቴጅዎችን ያካተተ ፖሊሲ ነበር፡፡

እነዚህን የትኩረት መስኮችና አቅጣጫዎች በመተግበር አገራችን ያላትን በርካታ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶችን በመጠቀም ፈጣን እና ቀጣይነት ያለው ዕድገትን ለማረጋገጥ በተደረገው ጥረት የቱሪዝም ዘርፍ የበኩሉን ሚና እንዲያበረክት አዎንታዊ ሚና ተጫውቷል፡፡ ነባር መስህቦችን በማጠናከር፣ አዳዲስ መስህቦችን በማልማት እንዲሁም መዳረሻዎችን በማሻሻል በኩል ጅምር ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል በሚያስችል መልኩ ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ የሆኑ መሠረተ-ልማቶችን እንዲሁም ምርትና አገልግሎቶችን በማስፋፋት ረገድ አበረታች ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ሽፋን እንዲጨመር፣ ብርቅየ የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥበቃ እንዲደረግላቸው፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች በዩኔስኮ (UNESCO) እንዲመዘገቡ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ እንዲሁም ጥገና እንዲደረግላቸው ጥረቶች ተደርጓል፡፡

አገልግሎት ሰጭ ተቋማት እንዲስፋፉ እና ዓለም አቀፍ መለያ/ብራንድ ያላቸው ሆቴሎች ወደ አገራችን ገብተው አገልግሎቶች እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በዘርፉ የሚሰጡ የአገልግሎቶችን ጥራት ለማሻሻል የደረጃ ምደባና የብቃት ማረጋገጫ ስርዓት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይል ሽፋን እንዲያድግና ዘርፉ ቀደም ብሎ የነበረበት ከፍተኛ የሰው ሃይል እጥረት እንዲቀንስ ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከቱሪዝም ግብይትና ማስተዋወቅ አንፃር “ምድረ ቀደምት” የተሰኘ አገራዊ መለያ/ብራንድ ተቀርፆ ኢትዮጵያን የማስተዋወቅና መለያውን የማስረፅ ስራዎች በውጭና በአገር ውስጥ በልዩ ልዩ መንገዶች ተከናውኗል፡፡ በዓለም አቀፍ የቱሪዝም ንግድ ትርዒቶች ተሳትፎ በማድረግ፣ የንግድ ለንግድ ትስሰሮችን በመፍጠር እንዲሁም መረጃዎችን በማሰራጨት የቱሪዝም ሃብቶች፣ መዳረሻዎቻች እና የኢንቨስትመንት እድሎች እንዲተዋወቁ ጥረት ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ ፖሊሲው የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ያልነበረው እና ግልፅ የአተገባበር ስልት ያልተበጀለት መሆኑ፣ ለዘላቂ የቱሪዝም ልማትና ተወዳዳሪነት የሰጠው ትኩረት አነስተኛ

መሆኑ፣ በዘርፉ ምቹ የኢንቨስትመንት ምህዳር አለመፈጠሩ እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስርዓቶች ጉድለት ያለባቸው መሆናቸው፣ በዘርፉ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው እና ዝቅተኛ መሆኑ፣ በቱሪዝም ተዋንያን መካከል ያለው ቅንጅት የላላ መሆኑ እንዲሁም የዘርፉ የማስፈፀም አቅም ዝቅተኛ መሆኑ፣ የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ ስራዎች ውጤታማ አለመሆን፣ ለአገር ውስጥ ቱሪዝም ልማት በቂ ትኩረት አለመሰጠቱ፣ ለአነስተኛና መካከለኛ የቱሪዝም ኢንተርፕራይዞች ምቹ ሁኔታ አለመፈጠሩ፣ ለዘርፉ ልማት የሚውል የፋይናንስ አቅርቦት ውስን መሆኑ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የቱሪዝም ትብብሮች ትኩረት ያልተሰጣቸው መሆኑ፣ በዘርፉ የተሰማራው የሰው ሃይል ተወዳዳሪነት ዝቅተኛ መሆኑ፣ የተፈጥሮና ባህላዊ ሃብቶች ጥበቃ እና አጠቃቀም ደካማ መሆኑ፣ በመዳረሻዎች የአካባቢ ማህበረሰብ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ውስን መሆኑ በግልፅ የተስተዋሉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ በሚፈለገው ደረጃ እንዳትተዋወቅ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት የቱሪዝም ተወዳዳሪነት ዝቅተኛ እንዲሆን፣ የቱሪዝም ምርቶች በዓይነትና በጥራት እንዳይስፋፉ፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዳይጠናከር እና የቱሪዝም ኢንቨስትመንት በሚፈለገው ደረጃ እንዳያድግ፣ የጎብኝዎች አገልግሎት ጥራት እንዳይረጋገጥ፣ የስራ እድሎች እንዳይስፋፋ፣ የጎብኝዎች ፍሰት እና የቱሪዝም ገቢ በሚፈለገው መጠን እንዳያድግ ብሎም ከዘርፉ የሚገኙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ምህዳራዊ ጥቅሞች ዝቅተኛ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ስለሆነም ዘርፉ ካለው አቅም አንፃር ሲመዘን ለጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት (GDP) ያለው አስተዋጽኦ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

በሌላ በኩል እንደ አገር የተፈጠሩ ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጦችን በአዲስ የፖሊሲ ማዕቀፍ ማስተናገድ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ በተፈጠሩ አገራዊ ለውጦች ምክንያት የቱሪዝም ዘርፍ ቅድሚያ ትኩረት ከተቸራቸው ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ዘርፉን ከአዳዲስ የፖሊሲ እይታዎችና አገራዊ የልማት ስትራቴጅዎች ጋር የተናበበ እንዲሆን ማስቻል ወሳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተፈጠሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ እና ሌሎች ለውጦች ጋር አብሮ የሚራመድ እና ተለዋዋጭ የሆነውን የቱሪዝም ዘርፍ ባህርይ ማስተናገድ በሚያስችል አግባብ የቱሪዝም ፖሊሲውን መከለስ የግድ ይላል፡፡

ስለዚህ በነባሩ ፖሊሲ አፈፃፀም ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት፣ የተፈጠሩ መልካም ዕድሎችን አሟጦ ለመጠቀም እና ተለዋዋጭ የሆነውን የቱሪዝም ዘርፍ ባህርይ በአግባቡ ለመምራት እንዲቻል በስራ ላይ የነበረውን የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ መከለስ አስፈልጓል፡፡

## 3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ መርሆች እና ዓላማዎች

### 3.1. የቱሪዝም ፖሊሲ ክለሳ አስፈላጊነት

የ2001 ዓ.ም የቱሪዝም ልማት ፖሊሲን መከለስ ያስፈለገበት መሰረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዘርፉን ለመምራት በ2001 ዓ.ም ተቀርፆ ሥራ ላይ በዋለው የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ የታዩ የፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎች እና የአፈፃፀም ክፍተቶችን በማረም ጊዜውን የዋጀ የፖሊሲ መርሆዎች፣ እይታዎችና አቅጣጫዎች ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

- መንግስት ለቱሪዝም ዘርፍ የሰጠውን ልዩ ትኩረት እና በኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ እንዲካተት የተደረገበትን እሳቤዎች እና የፖሊሲ እይታዎች ጋር እንዲጠጣም በማድረግ ለተሰጠው ትኩረት የሚመጥን የፖሊሲ አቅጣጫዎች በመንደፍ የቱሪዝም ዘርፉን በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር አስተሳስሮ መምራት እና ማልማት አስፈላጊ በመሆኑ፣
- ከዘርፉ ተለዋዋጭ ባህሪያት አንፃር የተከሰቱ ለውጦችን ለማስተናገድ እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችን እና የመልማት አቅሞችን በስፋት በመጠቀም የዘርፉን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ብሎም ለአገራዊ እድገት ጉልህ ሚና እንዲጫወት ለማስቻል፣
- አገራችን ያላትን ሰፊ የቱሪዝም ሃብቶች በሚገባ በመለየትና በማልማት መዳረሻዎች እንዲስፋፉ፣ የቱሪዝም ምርቶች እና አገልግሎቶች በዓይነት፣ በመጠንና ጥራት እንዲጎለብቱ እንዲሁም የቱሪዝም መሰረተ-ልማቶች እንዲጠናከሩ እና የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንትና ተሳትፎ እንዲያድግ በማድረግ ኢትዮጵያን ተመራጭ እና ተወዳዳሪ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ፣
- በጥናት ላይ የተመሰረተ ውጤት ተኮር የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ ስራዎችን በማጎልበት አገራችን በዓለም መድረክ ያላት ገፅታ እንዲገነባ፣ ከጎብኝ አመንጪ አገራት ጋር አስተማማኝ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር፣ የጎብኝዎች ፍሰት እና የገበያ ድርሻ እንዲጨምር ለማስቻል፣
- የዘርፉን እምቅ የመልማት አቅም በመጠቀም ተወዳዳሪ እና አካታች የቱሪዝም ልማትን በማረጋገጥ ፈርጀ-ብዙ አገራዊ ጥቅሞችን በማመንጨት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማስፈን፣
- የታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ሃብቶች እንዲጠበቁ እና በጥናትና ምርምር በተመሰረተ አኳኋን በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣
- በቱሪዝም ዘርፍ እና በሌሎች ዘርፎች መካከል ያለውን ግንኙነት እና ቅንጅት በማሳደግ፣ ትብብርን በማጎልበት፣ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም፣ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ጠንካራ የማስፈፀም አቅም መገንባት በማስፈለጉ ይህ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3.2. ርዕይ

በ2027 ዓ.ም ተወዳዳሪ እና ዘላቂ የቱሪዝም ልማትን በማረጋገጥ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀዳሚ የቱሪዝም መዳረሻ አገራት መካከል አንዷ ሆና ማየት፡፡

## 3.3. የፖሊሲው መርሆች

### 3.3.1. ትብብር እና አጋርነት

በቱሪዝም ልማት ውስጥ የዘርፉን ባለድርሻ አካላት ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ፣ ትብብር እና አጋርነት ማጠናከር የፖሊሰው ዋና መርህ ነው፡፡ በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተዋንያን የሚያደርጓቸው አስተዋፅዖዎች ትብብርን መሰረት ያደረጉና የተዋረደ ብሎም የጎንዮሽ ትስስርን ማዕከል ያደረገ መሆን ይገባዋል፡፡ በአገር አቀፍ፣ ቀጠናዊ፣ በአህጉር እና

በዓለም አቀፍ ደረጃዎች በዘርፉ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በጋራ ዓላማዎች ዙሪያ ጠንካራ ትብብርና አጋርነትን በሚያጠናክር መልኩ ይመራል፡፡

### 3.3.2. አካታችነት

የቱሪዝም ልማትን ለማረጋገጥ በማንኛውም የዘርፉ ዕቅድ እና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም የቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሀብቶች ባለቤት የሆኑ የሃይማኖት ተቋማትን፣ ባህላዊ ተቋማትን፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችን እና አካል ጉዳተኞችን ፍትሃዊ ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነት እና ተደራሽነት ለማረጋገጥ ይሰራል፡፡ በሁሉም የአገራችን ክፍሎች የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በፍትሃዊነት በማልማት እና በማስተዋወቅ የአካባቢ ማህበረሰቦች የጥቅሙ ተቋዳሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የቱሪዝም ልማት ስራዎች የጎብኝዎችን ልዩ ፍላጎት በተለይም ሁሉን አቀፍ ተደራሽነትን ያረጋገጡ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በመዳረሻዎች የሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ የቱሪዝም ንግድ ድርጅቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሚናቸውን እንዲያጠናክሩ በሚያደርግ መልኩ ፖሊሲው ይተገበራል፡፡

### 3.3.3. ዘላቂ የቱሪዝም ልማት

የቱሪዝም ልማት ስራዎች ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን እንዲሁም ስነ-ምህዳራዊ እና ማህበራዊ ፋይዳዎችን በሚያመነጭ መልኩ ይቃኛሉ፡፡ የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ቅርስ ጥበቃ፣ ጥገና፣ ምዝገባ፣ ልማት እና አጠቃቀምን ለማሳደግ በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በትኩረት ይመራል፡፡ ፖሊሲው ዘላቂ የቱሪዝም ልማትን ለማረጋገጥ የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ለማሻሻል የሚያስችል አቅጣጫ ይከተላል፡፡ ሃይማታዊና ባህላዊ ተቋማት ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሀብቶችን በመጠበቅ ረገድ በንቃት ይሳተፋሉ፤ ለዘላቂ የቱሪዝም ልማት ወሳኝ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ቱሪዝም ለቅርሶች ጥበቃ እና ለተፈጥሮ ሃብቶች እንክብካቤ አዎንታዊ ሚና እንዲኖረው ማድረግ ብሎም በዘርፉ ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ማህበራዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎችን መቀነስ የፖሊሲው ማጠንጠኛዎች ናቸው፡፡

### 3.3.4. ቴክኖሎጂ ተኮር የቱሪዝም ልማት

የቱሪዝም ዘርፍ ከቴክኖሎጂ ለውጦች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑና ተወዳዳሪነትን ከሚወስኑ አበይት ጉዳዮች አንዱ ቴክኖሎጂ በመሆኑ እንደ አገር የሚካሄዱ የቱሪዝም ልማት ስራዎች አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማመንጨት፣ ማላመድና መጠቀም ላይ ትኩረት ተደርጎ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅምን ለማላቅና የቱሪዝም እሴት ሰንሰለትን ለማጠናከር እንዲያስችል ፖሊሲው ቴክኖሎጂን ማዕከል ያደረገ የቱሪዝም ልማት አቅጣጫን ይከተላል፡፡

### 3.3.5. የአገልግሎት ልህቀት

ቱሪዝም በአመዛኙ በአገልግሎት ላይ የተመሰረተ ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን በእያዳንዱ የአገልግሎት እሴት ሰንሰለት ውስጥ በመልካም መስተንግዶ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ባህል መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በመንግስት፣ በግል ዘርፉ እና በሌሎች የቱሪዝም ዘርፍ ተዋንያን የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀልጣፋ እና ምቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ ብሎም በዘርፉ የሚሰጡ ሁሉም አገልግሎቶች ልህቀትን ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይተገበራሉ፡፡ ፖሊሲው የአገልግሎት ሰጭ

ተቋማት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው አገልግሎትን በመስጠት ዘላቂ እና ተወዳዳሪ የቱሪዝም ልማትን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ይተገበራል፡፡

### 3.4. የፖሊሲው ዓላማዎች

የቱሪዝም ዘርፍን ተወዳዳሪነትና ዘላቂነት በማሳደግ ፈርጀ-ብዙ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የፖሊሲው ዋና አላማ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የቱሪዝም ዘርፍ ለአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት እድገት፣ ለውጭ ምንዛሬ ገቢ እና ለስራ ፈጠራ የሚያበረክተውን ድርሻ ማላቅ፣
- የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማልማት እና ማስፋፋት፣
- የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ ቅርስ ጥበቃ፣ ልማት እና ዘላቂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣
- በቱሪዝም ልማት ዘርፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣
- የዘርፉን የአገልግሎት ጥራት ማሳደግ፣
- የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ ስራዎችን ውጤታማነት ማሳደግ፣
- በዘርፉ ብቁ የሰው ሀብት ማፍራት፣ ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣ ትብብር እና ስልታዊ አጋርነትን ማጠናከር፣

## 4. የፖሊሲው ዋና ዋና ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች

የቱሪዝም ዘርፉን ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ ስምንት ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡ እነዚህም የቱሪዝም መዳረሻ ልማት እና አስተዳደር፤ የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ ቅርሶች ጥበቃ እና አጠቃቀም፤ በቱሪዝም ዘርፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፤ የግል ዘርፉ ተሳትፎ፣ የአገልግሎት ጥራት ልህቀት፤ የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ፤ የቱሪዝም ዘርፍን አቅም መገንባት እንዲሁም ትብብር እና ስልታዊ አጋርነትን ማጠናከር ናቸው፡፡

### 4.1. የቱሪዝም መዳረሻ ልማት እና አስተዳደር

የቱሪዝም ፀጋዎችን በጥልቀት በመለየት እና በዘላቂነት የሚለሙበትን ሁኔታ በመዘየድ የቱሪዝም ምርቶችን ማልማት እና ማስፋፋት፣ ተወዳዳሪነትን ማጎልበት እና ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጠቀሜታዎች ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ዘርፉን በተሻለ መንገድ ለማሳደግ የቱሪዝም መሠረተ-ልማትን ማስፋፋት አንዱ የፖሊሲው ተልዕኮ ነው፡፡

የቱሪዝም መዳረሻዎችን ጥራት እና ተወዳዳሪነት በዘላቂነት ለማሳደግ የዘላቂነት አሰራሮችንና ስታንዳርዶችን በመተግበር የመዳረሻ አስተዳደርን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም በመዳረሻዎች የጎብኝዎችን ደህንነት በመጠበቅ የሰመረ የጉብኝት እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው የሚያስችል የጎብኝዎች ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋት የጎብኝዎችን ደህንነት ማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ በሌላ በኩል በቱሪዝም መዳረሻ አካባቢ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም በቱሪዝም ምክንያት የሚመጡ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን መከላከልና መቀነስ ያስፈልጋል፡፡

#### 4.1.1. የቱሪዝም ምርቶችን ማልማት እና ማስፋፋት

በነባሩ ፖሊሲ የቱሪዝም ፀጋዎች እና የመልማት ዕድሎችን በጥናት በመለየት የቱሪዝም ሃብቶችን በተቀናጀ መልኩ በዘላቂነት ለማልማት የሚያስችሉ የመዳረሻ ልማት ፕሮግራሞችን በመተግበር ረገድ የተስተዋሉ ክፍተቶች በዘርፉ ለሚጠበቀው መልካም አፈፃፀም እንቅፋት ሆነው ቆይተዋል። ያሉንን ዓይነተ-ብዙ የቱሪዝም ሀብቶች በመጠቀም ውጤታማና የተቀናጀ ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ስትራቴጂን በመተግበር የቱሪዝም ሀብቶች እንዲለሙ የሚያስችል የፖሊሲ ሽፋን አልነበረም። ስለሆነም ልዩ ልዩ የቱሪዝም ፀጋዎችን መነሻ በማድረግ የተለያዩ የቱሪዝም ዓይነቶችን በማልማት፣ ነባር የቱሪዝም ሀብቶች እና መዳረሻዎች ላይ ዕሴት በመጨመር፣ በገበያ ፍላጎት ላይ በመመስረት ያሉን የቱሪዝም ዓይነቶች እንዲጠናከሩ እንዲሁም አዳዲስ የቱሪዝም ዓይነቶች እንዲለሙ በማድረግ ዘርፉ ያለውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ በማሳደግ በኩል የተሰራው ስራ ዝቅተኛ ነው። በዘርፉ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ለማሳደግ ልዩ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዞኖች ባለመከለላቸው ምክንያት የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዕድሎችን በአግባቡ መጠቀም አልተቻለም። ለኹነት ቱሪዝም ሰፊ የልማት እድል ያለን ቢሆንም በልዩ ትኩረት እንዲለማ በማድረግ በኩል ክፍተቶች ይስተዋላሉ። በተጨማሪም የቱሪዝም ገበያን የወቅታዊነት (Seasonality) ክፍተት ለመቅረፍ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ አሰራሮችን መተግበር እና ተጨማሪ የቱሪዝም ምርቶችን ማልማት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

1. አገር አቀፍ የቱሪዝም ፀጋዎችና የመልማት ዕድሎች በጥናት ይለያሉ፤ ሃብቶቹን በተቀናጀ መልኩ በዘላቂነት ለማልማት የሚያስችሉ የመዳረሻ ልማት ፕሮግራሞች እና የልማት ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ይተገበራሉ።
2. የዘርፉን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ልዩ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዞኖች እንዲከለሉ እንዲሁም ለቱሪዝም ልማት ልዩ ኮሪደሮች/ማዕከላት እንዲመሰረቱ ይደረጋል።
3. ያሉንን ዓይነተ-ብዙ የቱሪዝም ሀብቶች በመጠቀም ውጤታማና የተቀናጀ የቱሪዝም መስመሮች (Tourism Circuits) ይዘረጋሉ፤ ክልሎች ያሏቸንውን የጋራ የቱሪዝም ሀብቶች በትብብር እንዲያለሙ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።
4. አገራዊ ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ይተገበራል።
5. ያሉንን የቱሪዝም ፀጋዎች መነሻ በማድረግ የተለያዩ የቱሪዝም ዓይነቶችን ለማልማት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች እና አሰራሮች ተዘጋጅተው ይተገበራሉ።
6. በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ እና ሌሎች ነባር የቱሪዝም ሀብቶችንና መዳረሻዎችን መሰረት በማድረግ ዕሴት የሚጨምሩ ልዩ ልዩ የቱሪዝም ኹነቶችን በማከናወን የበለጠ ተመራጭ እንዲሆኑ ይደረጋል።
7. ባሉን የቱሪዝም ፀጋዎች እና በገበያ ፍላጎት ላይ በመመስረት ነባር የቱሪዝም ዓይነቶች እንዲጠናከሩ እንዲሁም አዳዲስ የቱሪዝም ዓይነቶች እንዲለሙ ይደረጋል።
8. የመዳረሻ አካባቢን ባህል እና እሴት የሚያንፀባርቁ የስጦታ ዕቃዎች በየመዳረሻዎቹ በመጠን፣ በዓይነት እና በጥራት እንዲስፋፉ ይደረጋል። ባህላዊ የዕደ-ጥበብ መንደሮች እና ገበያዎች (Traditional Craft villages and markets) እንዲመሰረቱ ይደረጋል።

9. የቱሪዝም ገበያን የወቅታዊነት (Seasonality) ክፍተት ለመፍታት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
10. አገራችን ያላትን ዕምቅ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት የኹነት ቱሪዝምን (MICE- Meetings, Incentives, Conferences, and Exhibitions) በልዩ ትኩረት እንዲለማ እና እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡
11. መዝናኛን መሰረት ያደረገ (Leisure Tourism) የቱሪዝም ልማትና ሌሎች ቀደም ሲል አገራችን በአንፃራዊነት የምትታወቅባቸው የቱሪዝም ዓይነቶች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡
12. የቱሪዝምን ዘላቂነት በተለይም የአካባቢያዊ ዘላቂነትን (Environmental Sustainability) ከማላቅ አንፃር የዘላቂ ቱሪዝም ምርት ልማት የአሰራር ስርዓት ይዘጋጃል፤ ይህን ለሚያሟሉ የዘርፉ ምርትና አገልግሎት ሰጭዎች ዕውቅና ይሰጣል፡፡

### 4.1.2. የቱሪዝም መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት

አገራችን ያላትን በርካታ የቱሪዝም መስህቦችን ለመግለጥና የቱሪዝም ተጠቃሚነትን በጉልህ ለማሳደግ የቱሪዝም መሠረተ-ልማትን እና የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ማስፋፋት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ለቱሪዝም ልማት ወሳኝ የሆኑና የቱሪዝም መዳረሻዎችን የሚያስተሳስሩ መሰረተ-ልማቶች ጥናትን መሰረት ባደረገ መንገድ በማስፋፋት፣ ለአካባቢ ተስማሚ በማድረግ፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሴቶች፣ ለህጻናት እና ለሌሎች ልዩ እገዛ ለሚሹ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ምቹ ሆነው እንዲገነቡ በማስቻል ረገድ ነባሩ የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ ብዙም ትኩረት ካልሰጣቸው አንገብጋቢ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የኹነት ቱሪዝም መሰረተ-ልማቶች እና መገልገያዎችን በማስፋፋት፣ መዳረሻዎችን በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ እንዲሁም የጎብኝዎችን ምቾት በመጠበቅ በኩል ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡

በተጨማሪም ቀጠናዊ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎችን ከማሳለጥ አንፃር ከአጎራባች አገራት ጋር ያሉንን ድንበር ተሻጋሪ የቱሪዝም ሃብቶች ለማልማት የሚያስችል መሰረተ-ልማት በትብብር በመዘርጋት ረገድ ውስንነቶች ይስተዋላሉ፡፡

ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. ለቱሪዝም መስህቦችና መዳረሻዎች አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችና መገልገያዎች (የመናፈሻ ስፍራዎች፣ የመፀዳጃ ቤቶች፣ ዕረፍት ማድረጊያ ቦታዎች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የተፈጥሮ ሃብቶች መመልከቻ ማማዎች፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች፣ ወዘተ) ጥናትን መሰረት ባደረገ እና ስታንዳርዶችን በጠበቀ መልኩ እንዲገነቡ እና እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡
2. ማንኛውም የቱሪዝም መሰረተ ልማት ግንባታ ለአካባቢ ተስማሚ እና ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሴቶች፣ ለህጻናት እና ለሌሎች ልዩ እገዛ ለሚሹ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ምቹ ሆነው እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡
3. በአገራችን የተለያዩ ከተሞች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የኹነት ቱሪዝም (MICE Tourism) መሰረተ-ልማቶች እና መገልገያዎች (Facilities) እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

4. የቱሪዝም መዳረሻዎችን በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ እና የጎብኝዎችን ምቾት ለመጠበቅ ባለብዙ አማራጭ የትራንስፖርት ሥርዓት በትብብር እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡
5. ለቱሪዝም መዳረሻዎች አስፈላጊ የሆኑ የመንገድ፣ የመብራት፣ የውሃ፣ የቴሌኮም፣ የፋይናንስ እና የመሳሰሉ መሰረተ-ልማቶች እንዲሟሉ እና እንዲሻሻሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡
6. ቀጠናዊ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎችን ከማሳለጥ አንፃር ከአጎራባች አገራት ጋር ያሉንን ድንበር ተሻጋሪ የቱሪዝም ሃብቶች ለማልማት የሚያስችል የቱሪዝም መሰረተ-ልማት በትብብር ይዘረጋል፡፡

### 4.1.3. የመዳረሻ አስተዳደርን ማሻሻል

የቱሪዝምን ዘርፍ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ አዳዲስ ስልቶችንና አሰራሮችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የመዳረሻ ልማትና አስተዳደር ስራዎች የተፅዕኖ ግምገማ ጥናት መሰረት ባደረገ መንገድ ባለመሰራታቸው ምክንያት በስነ-ምህዳር እና ስነ-ሕይወት እንዲሁም በባህላዊ እሴቶች ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ማንኛውም የቱሪዝም ልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን የዘላቂ ቱሪዝም ፅንሰ-ሀሳቦችና መርሆችን ባገናዘበ እና ባዋሃደ መልኩ መተግበር ሲኖርበት ይህ ሳይሆን በመቅረቱ ሰፊ ጉድለቶች ተስተውለዋል፡፡ ስለሆነም የዘላቂ የቱሪዝም ልማት እና አመራርን ለማስተባበር የመዳረሻ አስተዳደር ድርጅቶችን በተለያዩ ደረጃዎች (በብሄራዊ፣ በክልል እና በወረዳ) መመስረት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የቱሪዝም መዳረሻዎች ጥራት እና ተወዳዳሪነትን በዘላቂነት ለማሻሻል ብሎም በመዳረሻዎች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር የመዳረሻ ልህቀት መለኪያ መስፈርቶች ተዘጋጅተው አልተተገበሩም፡፡ በመዳረሻዎች ቦታዎች የቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች ከሌሎች የልማት ዘርፎች ጋር እንዲተሳሰሩ በማድረግ የቱሪዝም እሴት ሰንሰለትን እንዲጎለብት እና የዘርፉ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ እንዲጠናከር በማድረግ ረገድ ሰፊ ክፍተት ነበር፡፡ ሀሉም የቱሪዝም ተዋንያን የሚመሩበት የስነ ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም የዘላቂነት አሰራሮችንና ስታንዳርዶችን በመተግበር የመዳረሻ አስተዳደርን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የቱሪዝም ልማት በመዳረሻዎች ያለውን አጠቃላይ የተጽዕኖ ግምገማ ጥናት በማድረግ የመዳረሻ ልማትና አስተዳደር ስራዎች እንዲሻሻሉ ይደረጋል፡፡
2. ዘላቂ የቱሪዝም ዕቅድ፣ ልማት እና አመራርን የሚያስተባብሩ የመዳረሻ አስተዳደር ድርጅቶች በተለያዩ ደረጃዎች (በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ) ይመሰረታሉ፡፡
3. የኢትዮጵያን የቱሪዝም መዳረሻዎች ጥራት እና ተወዳዳሪነት በዘላቂነት ለማሻሻል እና በመዳረሻዎች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር የመዳረሻ ልህቀት መለኪያ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡
4. ማንኛውም የቱሪዝም ልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን የዘላቂ ቱሪዝም ጽንሰ ሀሳቦችንና መርሆችን ባገናዘበና ባዋሃደ መልኩ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

5. በመዳረሻዎች የቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች ከሌሎች የልማት ዘርፎች ጋር እንዲተሳሰር በማድረግ የቱሪዝም እሴት ሰንሰለት እንዲጎለብትና የዘርፉ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡
6. በየመዳረሻዎች ያለውን የጉብኝት ስፍራዎች መግቢያ ዋጋ አወሳሰን ስርዓት ጥናትን መሰረተ ባደረገ መልኩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ይዘረጋል፤ ከሚገኘው ገቢ የተወሰነው ለአካባቢው ማህበረሰብ እና ለመዳረሻው ልማት እንዲውል ይደረጋል፡፡
7. የሰመረ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲኖር እና ዘላቂነት ያለው የቱሪዝም ልማት እንዲረጋገጥ የሚያግዝ የቱሪዝም የስነ-ምግባር መመሪያ ተቀርጾ ይተገበራል፡፡

### 4.1.4. የጎብኝዎችን ደህንነት ማረጋገጥ

በመዳረሻዎች የሰመረ የጉብኝት እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል የጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋት የጎብኝዎችን ደህንነት ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በነባሩ ፖሊሲ መዳረሻዎች ከፀጥታ እና ደህንነት አንፃር ያሉበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅድመ-መረጃ ስርዓት (Early Warning System) በማመላከት እና አደጋን ለመከላል የሚያስችል ለጎብኝዎች የቅድመ ጉዞ መረጃዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል ብሎም በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ጤና ነክ መረጃዎችን የሚያደርስ አስተማማኝ ስርዓት አልነበረም፡፡ በአጠቃላይ በታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ መስህቦችም ሆነ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት የጎብኝዎችን ደህንነት እንዲጠበቅ የሚያስችሉ ደረጃዎችን/ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. በመዳረሻዎች የጎብኝዎችን ደህንነት በመጠበቅ የሰመረ የጉብኝት እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው የሚያስችል የጎብኝዎች ጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ የጎብኝዎችን እና የማህበረሰብ ግንኙነትን (Host-Guest Relations) በማሳደግ ቀጣይነት ያለው የጎብኝዎች ደህንነት ጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
2. የቱሪዝም መዳረሻዎች ከፀጥታና ደህንነት አንፃር ያሉበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅድመ-መረጃ ስርዓት (Early Warning System) ይዘረጋል፡፡
3. የጤና አደጋን ለመከላል ለጎብኝዎች የቅድመ ጉዞ መረጃዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል፣ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ጤና ነክ መረጃዎችን የሚያደርስ አስተማማኝ ስርዓት ይዘረጋል፤ ችግር ሲፈጠር አፋጣኝ እገዛ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ይተገበራል፡፡
4. በመዳረሻ ስፍራዎች እና በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት የንፅህና እና ጤና አጠባበቅ ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ይደረጋል፤ የጤና እና ንፅህና አጠባበቅ ባህል እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡
5. የጀብድ ቱሪዝም (Adventure Tourism) በሚደረግባቸው ተፈጥሯዊ የጉብኝት ስፍራዎች (የውሃ ላይ ትርዒት፣ ተራራ መውጣት እና ዝላይ፣ ወዘት) የጎብኝዎችን ደህንነት እንዲጠበቅ የሚያስችሉ ስታንዳርዶችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ይተገበራሉ፡፡

### 4.1.5. የማህበረሰብን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ

በቱሪዝም መዳረሻ አካባቢ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሁም ሃይማኖታዊ፣ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሀብቶች ባሉባቸው መዳረሻዎች ላይ የሃይማኖት ተቋማት በመስህብ አስተዳድር ዙሪያ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንዲሁም ከዘርፉ ልማት ፍትሃዊ የጥቅም ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ አካል ጉዳተኞችን፣ ሴቶችን እና ወጣቶችን በቱሪዝም እንቅስቃዎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ አሰራሮችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. ቱሪዝም ለዘላቂ የገጠር ልማት የሚኖረውን አስተዋጽ ለማሳደግ እንዲቻል አነስተኛና መካከለኛ የንግድ ተቋማት እንዲፈጠሩ በማድረግ የገጠሩን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በትኩረት ይሰራል፡፡
2. በቱሪዝም መዳረሻ አካባቢ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሁም ሃይማኖታዊና ባህላዊ ተቋማት በመስህብ አስተዳድር ዙሪያ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡
3. በቱሪዝም መዳረሻዎች አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ በዘርፉ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ምርት እና አገልግሎቶችን ለጎብኝዎች እና ለቱሪዝም አገልግሎት ሰጭዎች እንዲያቀርቡ በማድረግ ከዘርፉ ልማት የጥቅም ተካፋይ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
4. በቱሪዝም መዳረሻዎች አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችሉ የስልጠና፣ የፋይናንስ እና ሌሎች ድጋፎችን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡
5. የማህበረሰብ-አቀፍ ቱሪዝም የሚስፋፋበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
6. የአካባቢ ማህበረሰቦችን በኢኮቱሪዝም ልማት ስራዎች ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡
7. የአካል ጉዳተኞችን፣ ሴቶችን እና ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ አሰራሮች ይተገበራሉ፡፡
8. ቱሪዝም በአካባቢው ማህበረሰብ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ሌሎች እሴቶች ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች በትኩረት ይሰራሉ፡፡

## 4.2. የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ ቅርሶች ጥበቃ እና አጠቃቀም

የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ቅርሶች የቱሪዝም ልማት መሰረቶች በመሆናቸው ምክንያት ለዘላቂ የቱሪዝም ልማት መረጋገጥ ወሳኝ ድርሻ አላቸው፡፡ የእነዚህን በዋጋ የማይተመኑ ቅርሶች ጥበቃ፣ ጥገና፣ ምዝገባ እና ዘላቂ አጠቃቀምን በማሳደግ ቀጣይነት ያለው የቱሪዝም ዕድገትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ቅርሶች ዘለቄታዊ አጠቃቀምን ለማሳደግ የመዳረሻ አካባቢውን ማህበረሰብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መንገድ ልማቶችን መፈፀም ያስፈልጋል፡፡

ቅርሶችን በአግባቡ በመጠበቅ እና ኃላፊነት የተሞላበት አጠቃቀምን በማሳደግ ብሎም የቱሪዝም ልማቶች የአካባቢን ባህል እና ብዝሃ-ህይወት በመጠበቅ ለትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ

አንዱ የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ የቅርሶች ጥበቃ፣ ጥገና፣ ምዝገባ እና ዘላቂታዊ አጠቃቀም ከቱሪዝም ልማት ጋር ማዋሃድ የዘርፉን ልዩ እሴት የሚያጎለብት ተግባር ነው፡፡

### 4.2.1. የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ቅርሶችን ጥበቃ ማሳደግ

ቅርሶችን በአግባቡ መጠበቅ እንዲቻል የቅርሱ ተቀዳሚ ባለቤት የሆነው የአካባቢው ማህበረሰብ እና ሃይማታዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብቶች ባሉባቸው መዳረሻዎች የሚገኙ ሃይማኖታዊ ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የቅርስ ምዝገባ፣ ጥገና፣ አጠቃቀም እንዲሁም ክትትልና ግምገማ ስራዎች ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በቅርሶች ላይ የሚደረጉ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ብሎም ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመከላከል አስፈላጊ የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመፈፀም ረገድ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡

የጥበቃ ስፍራዎች ሽፋን እንዲያድግ፣ የተጎዱ ቦታዎች እንዲያገግሙ፣ የብዝሃ-ሕይወት መመናመን እንዲቀንስ እና አደጋ ውስጥ ያሉ ብርቅዬ እንስሳትና ዕፅዋት ቁጥር እንዲጨምር የሚያስችሉ ስራዎች በሚፈለገው መጠን አልተፈፀሙም፡፡ በቅርስ ጥበቃ እና ጥገና ዘርፍ ሰፊ የሆነ የእውቅት ክፍተት አለ፡፡ በተጨማሪም በግጭት እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ለሚገኙ ቅርሶች የሚደረገው የጥበቃ ስራ ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎችን መሰረት ባደረገ መንገድ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከል እና ቅርሶችን ለመታደግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በማዘጋጀት መተግበር ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ ወቅቶች የተዘረፉ እና በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገራት የወጡ በርካታ የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ቅርሶችን የማስመለስ ስራ ወጥነት በሌለው መንገድ ሲፈፀም ቆይቷል፡፡

ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. ቅርሶችን በአግባቡ መጠበቅ እንዲቻል የቅርሱ ተቀዳሚ ባለቤት የሆነዉ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ተቋማትን እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ የቅርስ ምዝገባ፣ ጥበቃ እንዲሁም ክትትልና ግምገማ ስራዎች የሚመራበት ስትራቴጂና የአሰራር ሥርዓት ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡ ይህ ስራ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
2. የቅርሶች ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ጠብቀውና ዓለም አቀፍ የቅርስ ጥገና መርሆችና አሰራሮችን በተከተለ መልኩ ጥገና እና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ ለዚህም ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
3. በቅርሶች ላይ የሚደረጉ ህገ-ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይተገበራሉ፡፡
4. የአገር በቀል ዕውቀቶችን እና ውጤታማ ተሞክሮዎችን በአግባቡ በመለየት ለዘላቂ የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ቅርሶች ጥበቃና ልማት እንዲውሉ ይደረጋል፡፡
5. አገር በቀል የቅርስ ጥገና እውቀቶችን በማጎልበትና ከሳይንሳዊ አሰራሮች ጋር በማስተሳሰር በዘርፉ የበቁ የቅርስ ጥገና ባለሙያዎችን ለመፍጠር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

6. በግጭት እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ለሚገኙ የታሪክ፣ የባህል፣ የሃይማኖት እና የተፈጥሮ ቅርሶች ጥበቃ ስራዎች ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎችን መሰረት ባደረገ መንገድ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከል እና ቅርሶችን ለመታደግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡

7. የጥበቃ ቦታዎች ሽፋን እንዲያድግ፣ የተጎዱ ቦታዎች እንዲያገግሙ፣ የብዝሐ ሕይወት መመናመን እንዲቀንስ እና አደጋ ውስጥ ያሉ ብርቅዬ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት ቁጥር እንዲጨምር የሚያስችሉ ስራዎች በትኩረት ይሰራሉ፡፡ የዱር እንስሳት ጥናት እና ምርምር ስራዎችን ለማጎልበት እና የተፈጥሮ ሃብቶችን ጥበቃ ለማሳደግ ይሰራል፡፡

8. የህብረተሰብ ተሳትፎን በማጎልበት በዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች ላይ የሕግ ማስከበር ሥራዎችን ለማጠናከር የሚያግዝ የሕግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፡፡

9. አገራችን ያላትን እምቅ የስነ ምድር ሀብቶች በአግባቡ ለማልማት እና ለመጠቀም የስነ-ምድር ቅርስ ቦታዎችን (Geoheritage sites) እንዲጠበቁ እና ጂኦፓርኮች (Geoparks) እንዲስፋፉ ይደረጋል፤ አስፈላጊው የሕግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፡፡

10. በተለያዩ ወቅቶች የተዘረፉና በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ውጭ አገራት የወጡ በርካታ የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ቅርሶችን የማስመለስ ስራ ቅርሶቻችን በሚገኙበት አገር ያሉ ኤምባሲዎች እና ቆንስላዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ኢትዮጵያውያንን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ይሰራል፡፡

11. ህገ-ወጥ የቅርስ ዝውውርን ለመከላከል ከዓለም አቀፍ አካላት ጋር ትብብር ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ቅርስን የተመለከቱ አለም ዓቀፍ ስምምነቶች እንዲፈፀሙ ክትትል ይደረጋል፡፡

12. የአየር ንብረት ለውጥ በቅርሶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲሁም ቱሪዝም በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

### 4.2.2. የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ቅርሶችን ዘለቄታዊ አጠቃቀም ማሳደግ

የታሪክ፣ የባህል እና የተፈጥሮ ቅርሶች ዘለቄታዊ አጠቃቀም ለማሳደግ በሚያስችል መንገድ ሀብቶችን ማልማት ለቱሪዝም እድገት አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የእነዚህን ሀብቶች ዘላቄታዊ አጠቃቀም ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በመምራት እና ውጤት በማስመዝገብ ረገድ የሚፈለገውን ስኬት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ የሚካሄዱ የልማት ስራዎች/ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት የአካባቢያዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የቅርስ ተፅዕኖ ግምገማ እና የማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማዎችን በማካሄድ የሚኖራቸው አሉታዊ ተፅዕኖ በጥናት ተለይቶ እና በቅድሚያ ታስቦበት የሚሰራው ስራ አነስተኛ ነው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የባህል፣ የታሪክ እና የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲሁም ሃይማኖታዊ የሆኑ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሀብቶችን ዘላቄታዊ አጠቃቀም ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይዘጋጃል፡፡

2. በአገራችን የሚገኙ የቱሪዝም መስህብ ሀብቶችን በዘላቂነት ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና አጠቃቀሙን ለማሳደግ የሚያስችል የጥናት እና ምርምር ስራዎች እንዲጎለብቱ ይደረጋል፡፡
3. በአገሪቱ የሚካሄዱ የልማት ስራዎች/ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት የአካባቢያዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የቅርስ ተፅዕኖ ግምገማ እና የማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ስራዎች ይተገበራሉ፡፡
4. የተፈጥሮ ሃብቶች በተለይም የውሃ ሃብቶችን ከሌሎች የልማት ስራዎች ጋር በተሳሰረ እና በተናበበ መንገድ ለቱሪዝም ዘርፍ ዘላቂ አጠቃቀም ለማዋል የሚያስችል የአሰራር ማዕቀፍ ይዘረጋል፡፡
5. በታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና የተፈጥሮ ቅርሶች ላይ ሊደርሱ ስለሚችሉ ድንገተኛ አደጋዎች እና ቀውስ አፈታት፣ ስለ ባህልና የተፈጥሮ ቅርሶች ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲሁም የቱሪዝም ልማትን የተመለከቱ የግንዛቤ ፈጠራ እና የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፡፡
6. በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች የኢኮቱሪዝም ልማትን በማጠናከር ሃብቶች በአግባቡ ተጠብቀው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞችን እንዲያመነጩ ይደረጋል፡፡
7. የባህል፣ የታሪክ እና የተፈጥሮ ቅርሶች ዘላቂታዊ አጠቃቀም ለማሳደግ ሙዚየሞች (የዲጅታል ሙዚየሞችን ጨምሮ) እንዲስፋፉ ብሎም አገልግሎታቸውን በማላቅ ዘላቂ ገቢ እንዲያመነጩ ይደረጋል፡፡

### 4.3. በቱሪዝም ዘርፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ነባሩ የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ በዘርፉ ያለውን የቴክኖሎጂ እድሎችና የዲጂታል ኢኮኖሚ አቅም በበቂ ሁኔታ መጠቀም የሚያስችል የፖሊሲ ሽፋን አልነበረውም፡፡ ስለሆነም የዘርፉን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥ የቱሪዝም ቴክኖሎጂ ፈጠራን በማጎልበት፣ ዘመናዊ መዳረሻዎችን በማልማት እና በማስተዋወቅ የቱሪዝምን አቅም ለማሳደግ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል፡፡

#### 4.3.1. የቱሪዝምን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ተግባራዊነት ማረጋገጥ

የቱሪዝም ዘርፉን ከመሰረቱ ለማዘመን የሚያስችል የዲጅታል ቱሪዝም ፍኖተ-ካርታ ባለመኖሩ ምክንያት የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ ስራዎች በሚፈለገው ልክ ውጤታማ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የጎብኝዎችን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለማሳለጥ እና እርካታን ለመጨመር እንዲሁም የመዳረሻ ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል ብሎም አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችን እና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የዲጂታል ቴክኖሎጂ ውጤቶች በስፋት እንዲተዋወቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም በዘርፉ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ዕውቀትን እና አጠቃቀምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች በትኩረት ማከናወን ተገቢ ነው፡፡ የቱሪዝም የሰው ሀይል ገበያ መረጃዎች በአገር አቀፍ የስራ ገበያ መረጃ ስርዓት (Labor Market Information System) እንዲጠናከሩ በማድረግ በጥራት የተደራጀ መረጃዎችን ማመንጨት እና ለላቀ የመረጃ ትንተና የሚውል፣

በመረጃ ላይ የተመሰረተ እቅድ ለማውጣት የሚያስችል የመዳረሻ መረጃ አያያዝ ስርዓት (Destination Management Information System) መዘርጋት ለዘርፉ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የቱሪዝም ዘርፉን ከመሰረቱ ለማዘመን የሚያስችል የዲጅታል ቱሪዝም ፍኖተ-ካርታ ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡
2. የቱሪዝም ግብይትና ማስተዋወቅ ስራዎችን ውጤታማነት ለማሳደግ፣ የጎብኝዎችን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለማሳለጥ እና እርካታን ለመጨመር እንዲሁም የመዳረሻ ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል የዲጂታል ቴክኖሎጂ ውጤቶች በስፋት እንዲተዋወቁና እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡
3. የቱሪዝም ዘርፉን የሚያሳልጡና ተወዳዳሪነትን የሚያጠናክሩ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችንና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመደገፍ የሚስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡
4. በዘርፉ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ዕውቀትን እና አጠቃቀምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች በትኩረት ይከናወናሉ፡፡
5. ጊዜውን በዋጁ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የተደራጁ የቱሪዝም መዳረሻዎችን (Smart Tourism Destinations) ለመፍጠርና ለማስፋፋት በትኩረት ይሰራል፡፡
6. ዘርፉ በተጠና መልኩ በሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence) ቴክኖሎጂ እንዲጠናከር ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡
7. የቱሪዝም ዘርፍ የስራ እና የሰው ሃይል መረጃዎች በአገር አቀፍ የገበያ መረጃ ሥርዓት (Labor Market Information System) ውስጥ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡
8. በጥራት የተደራጀ፣ ለላቀ የመረጃ ትንተና የሚውል፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ እቅድ ለማውጣት የሚያስችል እና የመዳረሻ ልማት እንዲሁም ለማስተዋወቅ ስራዎችን የሚደግፍ የመዳረሻ መረጃ አያያዝ ስርዓት (DMIS-Destination Management Information Systems) ይዘረጋል፡፡
9. የቱሪዝምን የክፍያ ሥርዓት ለማዘመን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ እና ምቹ ዲጂታል የክፍያ ዘዴዎች እንዲሁም የጉዞ መተግበሪያዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡
10. የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለቀልጣፋ አገልግሎት እንዲጠቀሙ በማስቻል ቴክኖሎጅ ለዘርፉ እድገት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበርክት ይደረጋል፡፡
11. ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች የቱሪዝም ዘርፍ የሳይበር ደህንነት እና የጎብኝዎች መረጃ ጥበቃ ተግባርን በተመለከተ ዘርፉን ከሚመራው ተቋም ጋር በመተባበር ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ማዕቀፍ ይዘረጋል፡፡

### 4.4 የግል ዘርፉ ተሳትፎ

ዘርፉን በተሻለ መንገድ ለማሳደግ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ማስፋፋት አንዱ የፖሊሲው ተልዕኮ ነው፡፡ ስለሆነም የግል ዘርፉ በቱሪዝም ልማት የሚያደርገውን ተሳትፎ ማሳደግ እንዲሁም አቅማቸውን ማጠናከር ተገቢ ነው፡፡ ከአሁን ቀደም በነበሩ አሰራሮች የግል ዘርፉ

አቅም በሚፈለገው ደረጃ አልተገነባም። በመሆኑም ለዘርፉ ፈጣን እድገት ማበርከት የሚገባው ወሳኝ አስተዋፅዖ በሚፈለገው ደረጃ አይደለም።

### 4.4.1. የግል ዘርፍን ኢንቨስትመንት ማሳደግ

የዘርፉን ሁለንተናዊ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እና አገራዊ ፋይዳውን ለማጠናከር የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ልማትን ማሳደግ ተገቢ ነው። ከቱሪዝም ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ያሉ ነባር የሕግ ማዕቀፎች እና አሰራሮች ላይ አስፈላጊው ማሻሻያ ባለመደረጉ ምክንያት የአገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥታ የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ረገድ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። በዘርፉ የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር ባለመቀረፉ ምክንያት የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ተግባራትን በመግታት ረገድ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር የሚገኙ የገንዘብ ምንጮችን ገድቧል። በተጨማሪም የአገር ውስጥ ፍራንቻይዞች (Franchises) እንዲፈጠሩ፣ እንዲጠናከሩ እና ከኢትዮጵያ አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ አልተቻለም።

በነባሩ ፖሊሲ የቱሪዝም ዘርፉን ሁለንተናዊ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እና አገራዊ ፋይዳውን ለማጠናከር የሚያስችል ሰፊ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሥርዓት አልነበረም። በተጨማሪም ለአዳዲስ የቱሪዝም ዓይነቶች እና ከመሃል አገር ርቀው በሚገኙ ወይም መሰረተ-ልማት ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ልዩ የማበረታቻ ስርዓት አልተዘረጋም። ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

1. ከቱሪዝም ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ያሉ የሕግ ማዕቀፎችና አሰራሮች ላይ አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት እና የውጭ ቀጥተኛ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ይደረጋል።
2. የግል ዘርፉ በቱሪዝም ልማት አንቀሳቃሽ ሞተር መሆኑን በመገንዘብ በዘርፉ የሚያደረገውን ኢንቨስትመንት ለማሳደግ ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ እንዲፈጠር ይደረጋል።
3. በዘርፉ የሚስተዋለውን የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው የፋይናንስ ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል። የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን መደገፍ የሚያስችል የፋይናንስ ስርዓት እንዲዘረጋ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል።
4. በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ የአገር ውስጥ ፍራንቻይዞች (Franchises) እንዲፈጠሩ፣ እንዲጠናከሩና ከኢትዮጵያ አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ ይደረጋል።
5. የቱሪዝም ዘርፉን ሁለንተናዊ ተወዳዳሪነት ለማሳደግና አገራዊ ፋይዳውን ለማጠናከር የሚያስችል የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል። ለአዳዲስ የቱሪዝም ዓይነቶች እና ከመሃል አገር ርቀው በሚገኙ እና/ወይም ከፍተኛ የመሰረተ-ልማት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ልዩ የማበረታቻ ስርዓት ይቀረፃል።
6. ከግብር አከፋፈል ጋር ተያይዞ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ በመተባበር በጥናት ላይ ተመስርቶ የዘርፉን ተወዳዳሪነት በሚያጠናክር መልኩ እንዲሻሻሉ ብሎም ፍትሃዊ እና ወጥነት ያለው የግብር ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል።

7. የግል ዘርፉ የሚያደርገው ኢንቨስትመንት አረንጓዴ ልማትን የሚደግፍ እንዲሆን ይበረታታል፡፡ ለዚህም አሰራር ስርዓች ይዘረጋሉ፡፡

#### 4.4.2. የግል ዘርፉን አቅምና ተሳትፎ ማጠናከር

የግሉ ዘርፍ ለዘላቂና ተወዳዳሪ የቱሪዝም ልማት የራሱን ሚና እንዲወጣ ለማስቻል አቅማቸውን ማጠናከር እንዲሁም ተሳትፏቸውን ማሳደግ ይገባል፡፡ እስካሁን በነበረው የአገራችን የቱሪዝም ልማት የግል እና የመንግስት ትብብር ደካማ የሚባል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በግሉ ዘርፍ የተሰማሩ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ለቅርስ ጥበቃ፣ ለመሰረት ልማት ዝርጋታ እና ለሌሎች ጉዳዮች ያላቸው አስተዋጽኦ የሚጠበቀውን ያህል አይደለም፡፡ ለዚህ አንደኛው ምክንያት የግሉ ዘርፍ በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ያለውን ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረለትም፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

1. የመንግስት እና የግል ትብብርን (Public-Private Partnerships) በመመስረት የጋራ የቱሪዝም ልማት እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡ ትብብሩን የሚያጠናክሩ የህግ እና የማበረታቻ ማዕቀፎች ይዘጋጃሉ፡፡
2. የግሉ ዘርፍ በቅርስ ጥበቃ እና ልማት እንዲሁም በቅርስ ምዝገባ እና አስተዳደር ስራዎች ያለውን ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡
3. የግሉ ዘርፍ በመዳረሻ ልማት እና በመሰረተ-ልማት ዝርጋታ፣ በቱሪዝም ግብይትና ማስተዋወቅ፣ የሰው ሃይል ልማት እና ሌሎች የቱሪዝም ልማት ስራዎች ቁልፍ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
4. አነስተኛ እና መካከለኛ የቱሪዝም ንግድ ተቋማት እንዲጠናከሩ እና ወደ ከፍተኛ ተቋማት እንዲያድጉ የሚያስችል የአቅም ግንባታ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
5. የግል ዘርፉ አዳዲስ የንግድ ሃሳቦችን እንዲያመነጭ እና ወደ ተግባር ተለውጠው ለዘርፉ ፋይዳ የሚያመጡበትን ስርዓት በማበጀት የንግድ ፈጠራ (Entrepreneurship) ባህል እንዲዳብር ይደረጋል፡፡
6. የግል ዘርፉ ለቱሪዝም ልማት የተደራጀና ውጤታማ አስተዋፅዖ እንዲኖረው ለማስቻል አደረጃጀቶች ወይም ማህበራት እንዲጠናከሩ፣ ከዓለም አቀፍ የቱሪዝም ዘርፍ ተቋማትና ከሌሎች አገራት አቻ ማህበራት ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ድጋፍ ይደረጋል፡፡
7. ግሉ ዘርፍ የተሰማሩ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭዎች ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለመሰረት ልማት ዝርጋታ እና ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች የራሳቸውን ተቋማዊ ማኅበራዊ ኃላፊነት (Corporate Social Responsibility) እንዲወጡ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
8. ለግሉ ዘርፍ ባለራዕይ የሆኑ አመራሮችን እንዲሁም ተገቢው ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ለማፍራት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአጭር ጊዜ ተግባር ተኮር የአቅም ግንባታ ስልጠና ፕሮግራም ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይተገበራል፡፡

9. የግሉ ዘርፍ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት ምርጥ ተሞክሯዎቻቸውን እርስ በርስ የሚለዋወጡባቸው፣ ትስስር የሚፈጥሩባቸው እና ለጋራ ችግሮቻቸው በጋራ መፍትሄ የሚፈልጉባቸው መድረኮች እንዲዘጋጁ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

### 4.5 የአገልግሎት ጥራት

ለተወዳዳሪና ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ወሳኝ ከሆኑ ስራዎች መካከል አንዱ ለጎብኝዎች ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ የአገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ የአገልግሎት ሰጭዎችን ብቃት ማረጋገጥና በደረጃ መመደብ፣ አገልግሎት አሰጣጣቸውን መቆጣጠር እንዲሁም አቅማቸውን መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለዓለም አቀፍ ጎብኝዎች የላቀ አገልግሎት ለመስጠት ቪዛን ጨምሮ ወደ አገር ወስጥ ሲገቡ እና ከአገር ሲወጡ የሚያገኙትን አገልግሎት ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

#### 4.5.1 የብቃት ማረጋገጥ፣ የደረጃ ምደባ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ቁጥጥር እንዲሁም የድጋፍ ስራዎችን ማጠናከር

የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ብቃት ማረጋገጥና በደረጃ መመደብ የአገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ምንም እንኳ የብቃት ማረጋገጥና የደረጃ ምደባ ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ አዲስ ባይሆኑም ለተወዳዳሪና ዘላቂ የቱሪዝም ልማት እነዚህን ስራዎች ማጠናከርና ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡ በቱሪዝም ዘርፍ እየተሰጠ ያለው አገልግሎት የዘርፉን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት በሚያረጋግጥ መልኩ አይደለም፡፡ በነባሩ የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ መነሻነት ሆቴሎችን በደረጃ መመደብ እየተካሄደ ቢሆንም ይህ የደረጃ ምደባ ስራ አድሏዊነት በሌለበት እና ዓለም አቀፋዊነትን በጠበቀ መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ዘርፉ ብቃታቸው ሊረጋገጥ የሚገባ መደበኛ ያልሆኑ በርካታ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትም ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል የብቃት ማረጋገጥ መመሪያው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችን ወደ ኢንቨስትመንት እንዲመጡ የሚያበረታታ አይደለም፡፡ ዘርፉ ያሉበት ችግሮች ላይ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው ለአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ስታንዳርድ አለመዘጋጀት፣ የቱሪዝም ተቋማት ለጎብኝዎች የሚሰጡትን መሰረታዊ አገልግሎት እና የተመጣጠነ ዋጋ ክፍያን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖር፣ የአገልግሎት ደረጃዎችን አለመከተል እና ለአገር ውስጥ እና የገቢ መጠናቸው አነስተኛ ለሆኑ ዓለም አቀፍ ጎብኝዎች አገልግሎት የሚሰጡ የማረፊያ ተቋማት የአግልግሎት ጥራት ችግር ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. ህጋዊ እውቅና ያገኙ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ሽፋን/ቁጥር ለማሳደግ የሚያግዝ የማበረታቻ ስርዓት ተቀርጾ ይተገበራል፡፡
2. የቱሪዝም ብቃት ማረጋገጥ መስፈርቶችና መመሪያዎች የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ የሚያልቁ እና በዘርፉ እውቀት፣ ልምድና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች እንዲሳተፉ የሚያበረታቱ እንዲሆኑ ይደረጋሉ፡፡
3. ተዓማኒነት እና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት የደረጃ ምደባ ሥርዓት በመዘርጋት የደረጃ ምደባ ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

የደረጃ ምደባ ከተሰራላቸው በኋላ አፈጻጸማቸው እየተገመገመ ዳግም ምደባ ይደረግላቸዋል፡፡

4. በደረጃ ምደባ ውስጥ መካተት ላልቻሉ ተቋማት ልዩ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡
5. ለእያንዳንዱ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ዘርፍ ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃ (Minimum Standard) የያዘ መመሪያ ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡
6. የመክፈል አቅማቸው ዝቅተኛ ለሆኑ የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ጎብኝዎች አገልግሎት ለሚሰጡ የማረፊያ ተቋማት የደረጃ መመደቢያ መስፈርት ወይም ማሟላት ያለባቸው ዝቅተኛ ደረጃ ይዘጋጃል፤ በሚገባ እንዲተገበር ክትትል ይደረጋል፡፡
7. የጎብኝዎች አገልግሎቶችን ጥራት ለማስጠበቅና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሻሻል እንዲሁም የተመጣጠነ ዋጋ (Value-for-Money) እንዲኖር ለማስቻል ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤ ክፍተቶች ሲኖሩ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል፡፡ ለክትትልና ቁጥጥር የሚያገለግሉ መስፈርቶች ወጥነት እንዲኖራቸው በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አካላት ይሰራጫሉ፡፡
8. አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በሚገነቡበት ወቅት ከዲዛይን ጀምሮ ግንባታቸው ተጠናቅቆ ስራ እስኪጀምሩ ድረስ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡
9. የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አሰራሮቻቸውን እንዲያሻሽሉ እንዲሁም የሚሰጧቸውን አግልግሎቶች ደረጃ እንዲያሳድጉ ለማገዝ ሁሉን አቀፍ የጥራት አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
10. የግሉ የቱሪዝም ዘርፍ፣ ማህበረሰቡ እንዲሁም ግለሰቦች እንዲደራጁ፣ ማህበራትን እንዲያቋቁሙ እና ለወከላቸው አካል ድምጽ እንዲሆኑ፣ በዘርፉ ያለውን የአገልግሎት ጥራት እንዲቆጣጠሩ እና ለዘርፉ የሙያ ዕድገት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ አስቻይ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

### 4.5.2 ጎብኝዎች ወደ አገር ሲገቡና ከአገር ሲወጡ የሚያገኙትን አገልግሎት ማሻሻል

ዓለም አቀፍ ጎብኝዎችን ወደ አገራችን ለመሳብ ወደ አገር ውስጥ ለመግባትና ለመውጣት ያለው ሂደት ቀላል፣ ቀልጣፋ እና ምቹ ሊሆን ይገባል፡፡ በርካታ አገራት የዓለም አቀፍ ጎብኝዎቻቸውን ቁጥር የሚጨምሩበት አንዱና ዋነኛው መንገድ የቪዛ ሂደቱን ምቹ እና ቀልጣፋ በማድረግ ነው፡፡ ምንም እንኳ በአገራችን ከቪዛ ጋር በተገናኘ በየጊዜው መሻሻሎች ቢኖሩም የዓለም አቀፍ ጎብኝዎችን ቁጥር ከመጨመር አንጻር አሁንም በቪዛ አሰጣጥ እና ጉምሩክ አሰራር ዙሪያ ብዙ መሻሻሎች መደረግ አለባቸው፡፡ የጉምሩክ፣ የኢሚግሬሽና የኤርፖርት አገልግሎቶችን አስተማማኝና ደንበኛ-ተኮር እንዲሆኑ ማስቻል የግድ ይላል፡፡ የጎብኝዎች ትራንስፖርት አሰጣጥም ቀልጣፋ እና ምቹ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ ስለዚህ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. ዓለም አቀፍ ጎብኝዎችን ወደ አገራችን የበለጠ ለመሳብ የቪዛ አሰራር ሂደት ቀላል፣ ቀልጣፋ እና ምቹ የማድረግ ስራ ከሚመለተው አካል ጋር በጋራ ይሰራል፡፡

2. የጉምሩክ አሰራር ሂደቶችና ሌሎች ከጎብኝዎች መግባትና መውጣት ጋር የተያያዙ አገልግሎት አሰጣጦች ጉዞን እንዲያቀላጥፉ፣ የአገር ደህንነትን ባመዛዘነ መልኩ እንዲሻሻሉ እና አገልግሎት አሰጣጡም ደንበኛ ተኮር እንዲሆን ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሰራል፡፡
3. በኤርፖርት ውስጥ በጎብኝዎች ዘንድ በጎ አመለካከትና ገጽታ የሚፈጥር አገልግሎት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
4. ለጎብኝዎች ቀልጣፋና ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡
5. አግባብነት ያላቸውን ህጎችና ደንቦች መሰረት ባደረገ መልኩ ጎብኝዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡና ሲወጡ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ፈጣን ምላሽ የሚያገኙበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

### 4.6 የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ

ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ተለዋዋጭነት እና የገበያ ውድድር ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት የገበያ ጥናትን መሰረት ያደረገ እና ተጨባጭ የገበያ መረጃዎችና ፍላቶችን የቃኘ ግብይትና ፕሮሞሽን ስራ ማከናወን ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መነሻነት የአገራችንን የቱሪዝም ሀብቶቻች ማስተዋወቅ፣ የቱሪዝም ገበያን ማስፋፋት እንዲሁም የገበያ ድርሻን ማሳደግ  ያስፈልጋል፡፡

### 4.6.1 የቱሪዝም ገበያን ማስፋፋት እና የገበያ ድርሻን ማሳደግ

ኢትዮጵያ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ስትነጻጸር ዝቅተኛ የሆነ የቱሪዝም የገበያ ድርሻ ያላት ሲሆን አብዛኛው የአገራችን የዓለም አቀፍ ገበያ ትኩረት ያደረገው ጥቂት እና ነባር ገበያዎች ላይ ነው፡፡

ስለሆነም መጭውን ጊዜ በአግባቡ የተረዳ የቱሪዝም ገበያ ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀትና የገበያ ድርሻን ማሰደግ ተገቢ ነው፡፡ የፖሊሲ ክለሳ ጥናቱ በዘርፉ የሚፈለገውን የገበያ ዓይነት በማብዛት እና የገበያ ድርሻን በመጨመር ረገድ በርካታ ውስንነቶች እንዳሉ ያመላከተ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ደካማ የገበያ ልየታ እና መረጣ፣ እንደ አገር ለኤክስፖርት ዘርፎች በሚደረጉ ልዩ የድጋፍ ማዕቀፍ  የቱሪዝም ዘርፉ እንዲደገፍ አለመደረጉ፣ ለኹነት ቱሪዝም እና ለስቶፕኦቨር ቱሪዝም የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን፣ ለአገር ውስጥ ቱሪዝም የተሰጠው ዝቅተኛ ትኩረት፣ ኤምባሲዎች እና ቆንስላ ፅ/ቤቶች ለዜጎቻቸው የሚያወጧቸው ያልተገቡ የጉዞ ክልከላዎች እና የገበያ ልማትና የማስተዋወቅ ስራዎችን ውጤታማነት መገምገም አለመቻል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. በጥናት ላይ በመመስረት መጭውን ጊዜ የተረዳ የገበያ ልማት ስትራቴጂ ተቀርፆ ይተገበራል፡፡ የሚዘጋጀው ስትራቴጂ ለኹነት ቱሪዝም እና ለስቶፕኦቨር ቱሪዝም ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡
2. አገራችን ባሏት የቱሪዝም ሃብቶችና ምርቶች እንዲሁም በጎብኝዎች ፍላጎትና ምርጫ መሰረት የገበያ ልየታ እና መረጣ ይካሄዳል፡፡ የገበያ ልየታና መረጣው የአገር ውስጥ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የዲፕሎማሲ ማህበረሰቦችን እና የውጭ አገር ጎብኝዎችን

(ነባር እና አዳዲስ የውጭ ጎብኝዎችን እንዲሁም ከትውልድ አገራቸው ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን) ያካተተ ይሆናል፡፡

3. የቱሪዝም ዘርፍ ለአገልግሎት ኤክስፖርት ወሳኝ ድርሻ እንደሚያበረክት በዚህ ፖሊሲ እውቅና የተሰጠው በመሆኑ ዘርፉ የውጭ ምንዛሬ ከማመንጨት አኳያ ያለውን እምቅ አቅም ለመጠቀም እንደ አገር ለኤክስፖርት ዘርፎች በሚደረጉ ልዩ የድጋፍ ማዕቀፍ እንዲደገፍ ይደረጋል፡፡
4. ኤምባሲዎች እና ቆንስላ ፅ/ቤቶች ለዜጎቻቸው የሚያወጧቸውን ያልተገቡ የጉዞ ክልከላዎች ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ እንዲሁም ለማረም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡ በትክክለኛ መረጃዎች ላይ ተመስርተው የሚወጡ የጉዞ ክልከላዎችና ማስጠንቀቂያዎች ሁኔታዎች ሲለወጡ እንዲስተካከሉ ክትትል ይደረጋል፡፡
5. የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለማህበራዊ አብሮነት፣ ለሰላም፣ ለጋራ መግባባት እና ለአገር ግንባታ መሳሪያነት እንዲውል የሚያግዝ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡
6. ኢትዮጵያውያን አገራቸውን እንዲጎበኙ ለማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ (ለምሳሌ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ሰራተኞቻቸውን በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የቱሪዝም መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ) የሚያበረታታ ስርዓት እንዲሁም ነባር አደረጃጀቶች (የአገርህን እወቅ ክበባትና የጉዞ ማህበራት) እንዲጠናከሩ እና በተለያዩ ተቋማት (በትምህርት ተቋማት፣ በመንግስትና የግል መስሪያ ቤቶች) እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡
7. ለአገር ውስጥ ጎብኝዎች እና የአገር ውስጥ ቱሪዝም ላይ ትኩረት አድርገው ለሚሰሩ አስጎብኝ ድርጅቶች፣ የጉዞ ወኪሎች፣ የጉዞ ማህበራት እና ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ምቹ ሁኔታ እና የማበረታቻ ስርዓት ይዘጋጃል፡፡
8. የገበያ ልማትና የማስተዋወቅ ስራ ውጤታማነት የሚገመገምበት የክትትልና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 4.6.2 የቱሪዝም ማስተዋወቅ ስራን ማጠናከር

ኢትዮጵያን የጎበኙ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ቁጥር በ2002/03 ዓ.ም ከነበረው 468,000 በ2016/17 ዓ.ም ወደ 1,295,372 አድጓል፡፡ ነገር ግን የጎብኝ ፍሰቱ በሚፈለገው ፍጥነት እየጨመረ አይደለም፤ በተወሰኑ ዓመታትም በተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ጫናዎች የቱሪስቱ ቁጥር ቀንሶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በአጠቃላይ ኢትየጵያን የሚጎበኙ ቱሪስቶች ቁጥር አገሪቱ ካላት የቱሪዝም አቅም ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

የፖሊሲ ትንተና ውጤቱ ከማስተዋወቅ አንጻር በርካታ ችግሮች እንዳሉ ያመላከተ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የማስተዋወቅ ስራው የአገራችንን ብቸኛ እና ልዩ መገለጫዎችን አጉልቶ ማሳየት አለመቻሉ፣ ለማስተዋወቅ ስራ ብዙ ዓይነት ዘዴዎችን አለመጠቀም፣ ደካማ የሆነ የዲጂታል የማስተዋወቅ ስራ፣ የጎብኝዎች ፍሰት ወቅታዊነት እና ጎብኝዎች የተወሰኑ የሚታወቁ ቦታዎች ላይ ትኩረት ማድረጋቸው፣ ልዩ መለያ (Branding) ለተለያዩ መዳረሻዎችና የቱሪዝም ዓይነቶች አለመዘጋጀቱ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ የግብይት ተወካይ ቢሮዎች አለመኖር፣ የተበታተነ የማስተዋወቅ ስራ፣ የመረጃ ማዕከላት አለመጠናከር

እና አለመስፋፋት፣ የፈጠራ ኢንዱስትሪው ለቱሪዝም ማስተዋወቅ ስራ መጠቀም አለመቻል እና የአገር ውስጥ ጎብኝዎች መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ የሚያስችል ጠንካራ የማስተዋወቅ ስራ አለመስራት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

1. በአለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የማስተዋወቅና ገፅታ ግንባታ ስራዎች የአገራችን ብቸኛ መገለጫዎችንና ልዩ ባህሪያትን ማዕከል ያደረጉ እና የኢትዮጵያን በጎ ገፅታ የሚያጎሉ እንዲሁም ከአሁን ቀደም በዓለም መድረክ የተሰጣትን አሉታዊ ገፅታ የሚቀይሩ እንዲሆኑ ይደረጋል።
2. የጎብኝዎችን ዓይነትና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ፈጠራ በተሞላባቸው የማስተዋወቂያ ዘዴዎች፣ በአገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ንግድ ትርኢቶች፣ ኤግዚቪሽኖችና መሰል ኹነቶች እንዲሁም በትውውቅ ጉዞዎች (Familiarization Tours) አማካይነት ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ ስራ በትኩረት ይከናወናል።
3. ለመዳረሻዎች (ለክልሎችና ከተሞች) እና ለተለያዩ የቱሪዝም ዓይነቶች (ለኹነት ቱሪዝም፣ ለኢኮቱሪዝም፣ ለጂኦቱሪዝም፣ ለምግብ ቱሪዝም፣ ወዘተ) አገራዊ ልዩ መለያን/ብራንድን መሰረት ያደረጉ እና ፈጠራ የተሞላባቸው ንዑስ ልዩ መለያዎች/ብራንዶች ይዘጋጃሉ።
4. ስለ ኢትዮጵያ ቱሪዝም ጠቃሚ፣ ትክክለኛና ወቅቱን የጠበቀ መረጃ የሚሰጥ፣ የቱሪዝም መስህቦችን እና የቱሪዝም ምርትና አገልግሎቶችን የሚያስተዋውቅ ተዓማኒ ዲጂታል የመረጃ ማዕከል ይመሰረታል።
5. ጎብኝዎች አዳዲስ ቦታዎችን እንዲጎበኙ፣ ለኹነት ቱሪዝም የመጡ ተሳታፊዎች መስህቦችን እንዲጎበኙ እና ዓመቱን ሙሉ የጎብኝ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል።
6. ታዋቂ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቱሪዝም ንግድ ትርኢት በኢትዮጵያ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።
7. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ኢትዮጵያን ለዓለም አቀፍ ጎብኝዎች (የዲያስፖራውን ማህበረሰብ ጨምሮ) የሚያስተዋውቁ የውጭ የቱሪዝም ግብይትና ማስተዋወቅ ቢሮዎች በተመረጡ አገሮች እንዲከፈቱ ይደረጋል።
8. ከመንግስትና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጣ የኢትዮጵያን ቱሪዝም የማስተዋወቅ ሥራዎችን የሚያስተባብር አገራዊ የቱሪዝም ቦርድ ይቋቋማል።
9. በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ እንደ አገር ያላትን ገጽታ ለመገንባት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ስራዎች በተቀናጀ መንገድ ይከናወናሉ።
10. ጥናትን መሰረት ባደረገ መልኩ ነባር የጎብኝዎች የመረጃ ማዕከላት እንዲጠናከሩ እንዲሁም አዳዲስ ማዕከላት በተመረጡ መዳረሻዎች እንዲከፈቱ ይደረጋል።
11. እንደ አጠቃላይ ህዝቡ በተለይ ደግሞ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች እንዲጎበኙ የተለያዩ የግንዛቤ ፈጠራ እና የማነቃቂያ ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ።

12. የፊጠራ ኢንዱስትሪው ለቱሪዝም ማስተዋወቅና ገፅታ ግንባታ ስራዎች ውጤታማ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል፤ በቱሪዝም መስህቦችና መዳረሻዎች ላይ ፊልምን ጨምሮ በአገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ስመ-ጥር የኪነ-ጥበብ ስራዎች እንዲቀረፁ በማድረግ አገራችንን የማስተዋወቅ ስራዎች በትኩረት ይከናወናል፡፡

## 4.7 የቱሪዝም ዘርፍ አቅም ግንባታ

ቱሪዝም የኢትዮጵያ አንዱ ቁልፍ የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን ለአገሪቱ ዕድገት የራሱን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ በቅድሚያ ዘርፉ ካለበት የአስተዳደር፣ የአመራር፣ የሰው ሀብት ልማት እና በመረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ከመስጠት አንጻር ያሉ ክፍተቶች መፈታት አለባቸው፡፡ ጠንካራ ተቋማትንና አሰራሮችን ከመፍጠር አንፃር የሚስተዋሉ ክፍተቶች ስልታዊ በሆነ መልኩ መፈታት ይኖርባቸዋል፡፡ ቱሪዝም የአገልግሎት ዘርፍ እንደመሆኑ አስፈላጊውን ልማትና እድገት ለማምጣት ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ደግሞ ብቁ የሰው ሀብት ማፍራት እና ተቋማዊ አቅምን መገንባት በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

### 4.7.1 የዘርፉን የሰው ሀብት ልማት ማሳደግ

ቱሪዝም ብዙ የሰው ሀብት ስምሪት የሚፈልግ ዘርፍ ነው፡፡ የዘርፉ ስኬታማነት በዋናነት ባለው የሰው ሀብት ጥራት ይወሰናል፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በቱሪዝም ዘርፍ ከተሰማራው ጠቅላላ የሰው ሀብት ውስጥ አብዛኛው በዘርፉ የሰለጠነ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ለቱሪዝሙ ዘርፍ ብቁ የሰው ሀብት ለማፍራት ስልጠናዎችና የአቅም ግንባታ ስራዎች እየተከናወኑ ቢሆንም ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ሀብት ከማፍራት አንጻር አሁንም ሰፊ ክፍተት አለ፡፡

የፖሊሲ ጥናት ውጤቱ እንደሚያመለክተው የሰው ሀብት ልማት ስልት አለመኖር፣ የአመራርና የቴክኒክ ክህሎት እና የእውቀት ማነስ፣ ፍላጎትን መሰረት ያላደረጉ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች፣ ጥራት ያለው ትምህርት የሚሰጡ እና ችግር ፈቺ ምርምር የሚሰሩ የልህቀት ማዕከላት አለመመስረት፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፕሮግራሞች ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣ የዘርፉ የትምህርትና ምርምር ስራ አቅም አለመጠናከር፣ ለዘርፉ የሚያስፈልገውን ተሰጥኦ ያለውን የሰው ሀብት መሳብ አለመቻል እና ዘርፉ በተማረ የሰው ሀብት አለመደራጀቱ ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. በዘርፉ ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት ላይ ተመስርቶ የዘርፉን የሰው ሀብት ጥራትና ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የቱሪዝም ዘርፍ የሰው ሀብት ልማትና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡
2. የዘርፉን የክህሎት ፍላጎትና አቅርቦት ጥምረት በየጊዜው የሚፈተሽበትና የሚገመገምበት እንዲሁም ክፍተቱ ተለይቶ የሚሞላበት አሰራር ይዘረጋል፤
3. ለመንግስት እንዲሁም ቅርሶችን ለሚያስተዳድሩ ሃይማታዊና ባህላዊ ተቋማት ባለራዕይ የሆኑ አመራሮችን እንዲሁም ተገቢው ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ለማፍራት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአጭር ጊዜ ተግባር ተኮር የአቅም ግንባታ ስልጠና ፕሮግራም ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይተገበራል፡፡

4. በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ባለሙያዎች በተለይም ለቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ስራ አስኪያጆች፣ ለሼፎች፣ ለግለሰብ አስጎብኝዎች፣ ለኹነት አዘጋጆች፣ ለአማካሪዎች፣ ወዘተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፕሮግራሞች (Professional Certification Programs) ተቀርጸው ይተገበራሉ፤ ክፍተቶች እየተለዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡
5. በዘርፉ የተሰማሩ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንዲጠናከሩ በማድረግ ጥራት ያለው የሰው ሃይል እንዲያፈሩ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በዘርፉ የልህቀት ማዕከላት እንዲስፋፉ ጥረት ይደረጋል፡፡
6. በደረጃ የሚታቀፉ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በሰለጠኑ ባለሙያዎች እንዲደራጁ እና እንዲመሩ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
7. የቱሪዝም ትምህርት በየደረጃው በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተካትቶ ለተማሪዎች እንዲሰጥ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

### 4.7.2 የዘርፉን ተቋማዊ አቅም ማሳደግ

ዘላቂ እና ተወዳዳሪ የቱሪዝም ልማትን ለማረጋገጥና ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ እንዲሁም አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ተቋማዊ አቅምን በሚመለከት በዘርፉ የሚስተዋሉ ዋና ችግሮች የመዋቅር አለመናበብ፣ ያልተደራጀ እና ደካማ የሆነ የመረጃ ልውውጥ፣ የሚዘጋጁ መድረኮች የተበታተኑ እና የዘርፉን አቅም በሚፈለገው አግባብ መገንባት አለመቻላቸው፣ ዘርፉ ላይ ትኩረት አድርጎ ችግር ፈቺ የምርምር ሥራ የሚሰራ ተቋም አለመኖር፣ ዘርፉ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ አደጋዎችን ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት አለመዘርጋት፣ በዘርፉ ደካማ የስራ ፈጠራ ባህል መኖር፣ ደካማ የማስፈጸም አቅም፣ የፋይናንስ እጥረት እና ብልጫ ያሳዩትን እና አርዓያ የሆኑ ቋማትን እውቅና የሚሰጥበት ወጥ አሰራር አለመኖር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

1. በፌደራል እና በክልል የመንግስት የቱሪዝም ዘርፍ ተቋማት መካከል ነባራዊ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ መዋቅራዊ መናበበ እና የሰመረ ቅንጅት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በቱሪዝም ዘርፍ ተቋማትና በሌሎች ዘርፍ ተቋማት መካከል ያለው መዋቅራዊ የስራ ግንኙነትና ቅንጅት እንዲጠናከር በትኩረት ይሰራል፡፡
2. የቱሪዝም ዘርፍ ተቋማዊ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ተቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
3. የፌዴራልና የክልል ተቋማት አምዳዊና የጎንዮሽ የጋራ ስራዎችን እና መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል በቴክኖሎጂ የታገዘ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
4. በቱሪዝም ዘርፍ የተጠናከረና አስተማማኝ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
5. የቱሪዝምን ማክሮ-ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ለመለካት እንዲቻል የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ስራ በየጊዜው ይከናወናል፡፡
6. የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት ምርጥ ተሞክሯዎቻቸውን እርስ በርስ የሚለዋወጡባቸው፣ ትስስር የሚፈጥሩባቸው እና ለጋራ ችግሮቻቸው በጋራ መፍትሄ የሚፈልጉባቸው የምርምር ኮንፈረንሶች፣ ወርክሾፖች እና ሌሎች መድረኮች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

7. በቱሪዝም ዘርፍ ጥናትና ምርምሮችን የሚያደርግ እና በጥናቶች መሰረት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የሚችል አገራዊ የቱሪዝም የምርምር ተቋም እንዲመሰረት ይደረጋል፡፡
8. የባለድርሻ አካላትን ሚና እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳይ እና ለአደጋ ቅድመ-ጥንቃቄ ለማድረግ፣ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ብሄራዊ የቱሪዝም ቀውስ መከላከል እና ማገገም ማስተር ፕላን እንዲዘጋጅ እና እንዲተገበር ይደረጋል፡፡
9. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አዳዲስ ሃሳቦችን ለማፍለቅ የሚያስችሉ፣ ልዩ ግኝቶችን እና ስራ ፈጠራን እንዲሁም ተግባር-ተኮር ምርምርን የሚያበረታቱ ብሄራዊ የሃሳብ ማበልጸጊያ እና ፈጠራ ማዕከላት እንዲመሰረቱ ይደረጋል፡፡
10. የመንግስትን የማስፈጸም አቅም ለማሳደግ ነባር የህግ ማዕቀፎችን የመከለስ፣ አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችን የመቅረጽ እና የማስፈጸም አቅምን የማሳደግ ስራዎች ይሰራሉ፡፡
11. የቱሪዝም ዘርፉን አቅም ለማጠናከር በአገር ዓቀፍ ደረጃ የቱሪዝም ልማት ፈንድ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡
12. በተለያየ ዘርፍ የላቀ ውጤት ላሳዩ እና አርዓያ ለሆኑ ግለሰቦችና ተቋማት የሽልማትና እውቅና አሰጣጥ ስርዓት ይዘረጋል፤ ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርግ አካል እንዲመሰረት ይደረጋል፡፡

## 4.8 ትብብር እና ስልታዊ አጋርነት

ቱሪዝም በባህሪው ከብዙ ዘርፎች ጋር የሚገናኝ በመሆኑ ውጤታማ ለመሆን የብዙ ባለድርሻ አካላትን ትብብር እና አጋርነት ይፈልጋል፡፡ የቱሪዝም ዘርፉ ለዘላቂ ልማት የሚኖረውን አቅም ለመጠቀም ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ፣ በዘርፎች መካከል ትስስር የሚፈጥር እና ስልታዊ አጋርነትን የሚያበረታታ ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና ትብብር ማሻሻል እና ከዓለም አቀፍ አካላት ጋር ስልታዊ አጋርነትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

### 4.8.1 የቱሪዝም ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና ትብብር ማሳደግ

የቱሪዝም አስተዳደር ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ለማሳተፍ እንዲችል ያልተማከለ ስርዓትን መከተል አለበት፡፡ ዘላቂ የቱሪዝም ልማት የመንግስትና የግሉን ዘርፍ እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ የፖሊሲ ጥናት ውጤቱ እንደሚያመለክተው ከዚህ በፊት በነበረው ፖሊሲ አፈጻጸም ዙሪያ ከነበሩ ዋና ዋና ክፍተቶች መካከል በተለያየ መስክ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና ትብብር አነስተኛ እና ደካማ መሆን፣ አስፈላጊ የትብብር አደረጃጀቶች አለመፈጠር እና የህግ ማዕቀፎች አለመኖር ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስለሆነም የቱሪዝም ባለድርሻ አካላትን ትብብር ለማሳደግ እና ባለብዙ ተዋናይ የአስተዳደር ስርዓትን ለመፍጠር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የቱሪዝም ባለድርሻ አካላትን በጋራ ጉዳይ ለማሳተፍ የሚያስችል የባለድርሻ አካላት የተሳትፎ ስትራቴጂ ይዘጋጃል፡፡

2. በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት (የግሉን ዘርፍ ጨምሮ) በስርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ በኢንተርንሽፕ፣ በኤክስተርንሽፕ እና በሌሎች ተግባር-ተኮር ስልጠናዎች የሚሳተፉበት የቱሪዝም ስልጠናና ትምህርት አስተባባሪ ፎረም ይመሰረታል፡፡
3. የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የያዘ የዘርፉን ቁልፍ ችግሮች እንዲፈቱ እና ዘርፉ በአግባቡ እንዲመራ የሚያደርግ የቱሪዝም ካውንስል በአገር አቀፍ፣ ክልል፣ ዞን እና ወረዳ/መዳረሻ ደረጃ ይቋቋማል፡፡
4. ዘርፉን በአግባቡ ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚያስችሉ አስፈላጊ የህግ ማዕቀፎች ይቀረጻሉ፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይተገበራሉ፡፡
5. የቅርስ ባለቤት የሆኑ የሃይማኖት ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ እንዲሁም የቱሪዝም ልማት ዙሪያ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

### 4.8.2 በዓለም አቀፉ ደረጃ ያሉ ስልታዊ አጋርነቶችን ማጠናከር

ዓለም አቀፍ ትብብርና አጋርነት ለተወዳዳሪነት እና ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ነባሩ የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ ለዓለም አቀፍ ትብብር እና አጋርነት ትኩረት የሰጠ አልነበረም፡፡ ቱሪዝምን ለውጭ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች እንደ አንድ ወሳኝ መሳሪያ ያለመጠቀም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ አካላት ጋር በተለያየ መስክ ትብብሮችን አለመፍጠር እና የተፈጠሩትን ማጠናከር አለመቻል እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ወደ አገራችን በማምጣት ጥቅም ላይ አለማዋል ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

ስለሆነም የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

1. ከተለያዩ አገራት ጋር በሚደረጉ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ቱሪዝምን እንደ አንድ ወሳኝ ኢኮኖሚያዊ እና ህዝባዊ የዲፕሎማሲ መሳሪያ አድርጎ በመጠቀም ዓለም አቀፍ ንግድንና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን እንዲደግፍ እንዲሁም የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን እንዲያጠናክር በማድረግ አገራዊ ተጠቃሚነትን የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡
2. ከተለያዩ አገራት መንግስታት እንዲሁም ከቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር በቱሪዝም ዙሪያ የሁለትዮሽና ባለብዙ ወገን ትብብሮች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡
3. ዘላቂ ቱሪዝምን ለማልማት እና ቅርሶችን ለመጠበቅ ከሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ አካላት ጋር ትብብር ይደረጋል፡፡
4. ቀጠናዊ የቱሪዝም ትስስርን ለማጠናከር ከአጎራባች አገራት ጋር ያሉንን ድንበር ተሻጋሪ የቱሪዝም ሀብቶች እንዲጠበቁ እና እንዲለሙ ይደረጋል፡፡
5. በቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮች እና መድረኮች ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ በጥናትና ምርምር፣ በምርት ልማት፣ በግብይትና ማስተዋወቅ፣ በስልጠና እና በፈጠራ ዘርፎች ምርጥ ተሞክሮዎችን ወደ አገራችን የማምጣት እና የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡
6. የግል ዘርፉ በተናጠልም ይሁን በተደራጀ መልኩ ከሌሎች አገራት የግል ዘርፍ ጋር በትብብር እንዲሰራ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡

## 5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች

የቱሪዝም ፖሊሲው ተግባራዊ ሲሆን የፖሊሲው ውጤታማነት የሚረጋገጥባቸው አምስት ቁልፍ የውጤት መስኮች እንደሚከተለው ተለይተዋል፡፡

### 5.1 ያደገ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት

በነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች ላይ እሴት በመጨመር፣ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማት፣ የቱሪዝም ምርቶችን ዓይነትና ብዛት እንዲሁም ጥራት በማሳደግ፣ የቱሪዝም መሰረተ-ልማትንና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት፣ የመዳረሻዎችን አያያዝና አስተዳደር በማሻሻል፣ የጎብኝዎችን ደህንነት በማረጋገጥ፣ የገበያ ልማት ስራን በማጠናከር፣ የማስተዋወቅ ስራን የሚደግፉ አደረጃጀቶችን በመፍጠርና በማስፋፋት፣ በተለያዩ እና በቴክኖሎጂ በታገዙ የማስተዋወቂያ ዘዴዎች የአገራችንን የቱሪዝም ሀብቶችና ምርቶች ለጎብኝዎች በማስተዋወቅ በዘርፉ የተደረገ ኢንቨስትመንት ዕድገት፣ የተፈጠሩ የስራ ዕድሎች ብዛት፣ የገበያ ድርሻ እድገት፣ ከዘርፉ የተገኘ ገቢ መጠን ዕድገት እና ዘርፉ ለጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ዕድገት የፖሊሲው የውጤት መገለጫዎች ተደርገው ተወስደዋል፡፡

### 5.2 ያደገ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች የጥበቃ እና አጠቃቀም ሁኔታ

የአካባቢውን ማህበረሰብ፣ የቅርሱ ባለቤት የሆኑ ሃይማታዊና ባህላዊ ተቋማትን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶችን መጠበቅና ማልማት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገላቸው ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ተፈጥሯዊ የመስህብ ቦታዎችና ቅርሶች ብዛት፤ ጥገና የተደረገላቸው ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ብዛት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ ቅርሶች ብዛት፣ እንዲያገግሙ የተደረጉ ተፈጥሯዊ የመስህብ ቦታዎች ብዛት፤ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ሽፋን ዕድገት፣ በአደጋ ውስጥ የነበሩና በእንክብካቤ አማካይነት ቁጥራቸው የጨመረ ዱር እንስሳት ብዛት እና ስለቅርሶች እንክብካቤና ጠቀሜታ ግንዛቤ የተፈጠረላቸው የማህበረሰብ አካላት ብዛት፣ በቅርሶች ላይ የሚካሄዱ ህገ-ወጥ ድርጊቶች መቀነስ እና የተሻሻለ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እንዲሁም የተፈጥሮ ቅርሶች የጥበቃ ሁኔታ የሚያመለክቱ ቁልፍ የውጤት መለኪያዎች ናቸው፡፡

### 5.3 ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ሃይል እና ጠንካራ ተቋማዊ አቅም

ፖሊሲው ውጤታማ እንዲሆን ከሚጠበቅባቸው መስኮች መካከል አንዱና ዋነኛው ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ሃይል መፍጠር እንዲሁም ጠንካራ ተቋማዊ አቅም መገንባት ነው፡፡ የዚህ ውጤት ዋና ዋና መገለጫዎች ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ሃይል ብዛት፣ የሰው ሃይል ውጤታማነት እንዲሁም ከሰው ሃይል ልማት ውጭ ያሉ ተቋማዊ አቅሞች ማጠናከርን ያካትታል፡፡ የሰው ሀብት ልማትና የአቅም ግንባታ ስልት ዝግጅት፣ የአጭር ጊዜ ተግባር ተኮር የአቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ የክህሎት ፍላጎትና አቅርቦት ጥምረት ማሻሻያ አሰራ ስርዓት፣ የሙያ አመራር ብቃት ማረጋገጫ ፕሮግራሞች፣ የትምህርት እና ምርምር ተቋማት የልህቀት ማዕከል ምስረታ ይተገበራሉ፡፡

የመረጃ ስርዓትን እና መዋቅርን የማጠናከር፣ የቱሪዝም አደጋ መከላከል ማስተር ፕላን በማዘጋጀት እና በመተግበር አደጋዎችን የመከላከልና አስተማማኝ ምላሽ የመስጠት አቅም

የመፍጠር፣ የምርምር ስራዎችን የማጠናከር፣ የሃሳብ ማበልጸጊያ እና ፈጠራ ማዕከላትን የመመስረት እንዲሁም የቱሪዝም ፈንድን የማቋቋም ስራዎች ይከናወናሉ:: እነዚህን ውጤቶች በማስመዝገብ ተልዕኮውን በብቃት የሚወጣና ዘርፉን የሚያንቀሳቅስ ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ሀብት የመፍጠር እንዲሁም ጠንካራ ተቋማዊ አቅም የመገንባት ሁኔታ የፖሊሲው አፈጻጸም የሚገመገምበት አንድ ውጤት አመላካች ተደርጎ ተወስዷል::

### 5.4 ያደገ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ትብብርና አጋርነት

ከባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስችሉ የተለያዩ አደረጃጀቶችንና የአሰራር ስርዓቶችን በመመስረት፣ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር እና ከዘርፍ ዘለል እና ከዓለም አቀፍ አጋር አካላት ጋር ስምምነቶችን በማድረግ የዘርፉን እድገት ማፋጠን ተገቢ ነው:: የእነዚህን ስራዎች ተግባራዊነት በማረጋገጥ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ትብብርና አጋርነት ዕድገት አንዱ የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት አመላካች ተደርጎ ተወስዷል::

### 5.5 የአገልግሎት ጥራት ልህቀት

የአገልግሎት ጥራት ልህቀት የዚህ ፖሊሲ አንዱ ቁልፍ የውጤት መገለጫ ነው:: የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጭዎች ብዛት፣ በደረጃ የተመደቡ አገልግሎት ሰጭዎች ብዛት፣ ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃ (Minimum standard) ያሟሉ ተቋማት ብዛት፣ የተሰጡ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችና ድጋፎች ብዛትና ጥራት፣ ቴክኖሎጂን ለምርት ልማት እና ለቀልጣፋ አገልግሎት የተጠቀሙ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭዎች ብዛት እና የዘርፍ ባለድርሻ አካላት ተሞክሮዎቻቸውን የሚለዋወጡባቸው መድረኮች ብዛት በማሳደግ የአገልግሎት ልህቀትን ማረጋገጥ እና የጎብኝዎችን እርካታ ማሳደግ አንዱ የፖሊሲው ውጤት መገለጫ ነው::

## 6. የቱሪዝም ፖሊሲ የማውጣት ስልጣን እና ወሰን

### 6.1 ፖሊሲ የማውጣት ሥልጣን

ይህ የቱሪዝም ፖሊሲ ክለሳ ስራ በቱሪዝም ሚኒስቴር ሃሳብ አመንጭነት የተዘጋጀ ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ተግባራዊ ይደረጋል::

### 6.2 የፖሊሲው ወሰን

ይህ ፖሊሲ በኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ልማትን የሚመለከት ሲሆን በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ለሚገኙ የቱሪዝም ፀጋዎች ልየታ እና ጥበቃ እንዲሁም አጠቃቀም፣ የቱሪዝም መዳረሻዎች ልማት እና አስተዳደር፣ በቱሪዝም ዘርፍ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን የማላቅ የአገልግሎት አሰጣጥን የማሻሻል፣ የቱሪዝም ግብይት እና ማስተዋወቅ፣ በቱሪዝም ዘርፍ የሰው ሃብትና ተቋማዊ አቅም ግንባታ እንዲሁም ስልታዊ አጋርነትን የማጠናከር ስራ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

## 7. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

### 7.1 ፖሊሲውን የሚያስፈፅሙ ተቋማት እና ኃላፊነት

ፖሊሲው በአግባቡ እንዲፈጸም የፖሊሲ አስፈጻሚ ክፍል (Policy Implementation Unit) በቱሪዝም ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ እንዲቋቋም ይደረጋል:: ይህ ክፍል ዝርዝር የፖሊሲ አፈጻጸም የድርጊት መርሃ ግብር የማውጣት፣ ስለፖሊሲው ግንዛቤ የመፍጠር እና ለአስፈጻሚ

አካላት አቅም የመገንባት፣ የፖሊሲውን አፈጻጸም እና ያበረከተውን አስተዋጽኦ ግምገማ የማስተባበር እና ስለአፈጻጸሙ ሪፖርት የማዘጋጀት፣ በፖሊሲ አፈጻጸም ዙሪያ በአገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ወደ ቱሪዝም ዘርፍ እንዲመጡ የማገዝ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ዋና ዋና ተግባራት የሚኖሩት ሲሆን ዝርዝሩ ተግባራቱ ወደፊት የሚወጣ ይሆናል፡፡

ከቱሪዝም ፖሊሲ አስፈጻሚ ክፍል በተጨማሪ ብሄራዊ የቱሪዝም ካውንስል እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ የካውንስሉ ዋና ተግባር የፖሊሲውን አፈጻጸም ማስተባበርና መከታተል ሲሆን አወቃቀሩን እና ዝርዝር ሃላፊነቱን የሚመለከት የሕግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የፌደራል ተቋማት፣ የክልል ተቋማት፣ የግል ዘርፉ፣ የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰብ እና የሲቪክ ማህበራት ሃላፊነቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

### 7.1.1 የፌደራል አስፈፃሚ አካላት ሃላፊነቶች

- ፖሊሲውን ወደ ተግባር ለመተርጎም የሚዘጋጁ የቱሪዝም ልማት ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች በጀት መመደብ፣ የዘርፉን ልማት የሚያፋጥኑ የፋይናንስ አቅርቦቶች ማመቻቸት፡፡
- በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የማስተዋወቅና የገጽታ ግንባታ ስራዎች፤ የቱሪዝም ገበያ ትስስሮች እንዲሁም ከአገራት እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የሚደረጉ የቱሪዝም ግንኙነቶች እንዲጠናከሩ ማድረግ፡፡ በቱሪዝም ዘርፍ የዲያስፖራው ተሳትፎ እንዲጠናከር ማድረግ፡፡
- ጎብኝዎች ወደ አገራችን ሲገቡና ከአገራችን ሲወጡ ውጤታማ የኤርፖርት እና ኤሚግሬሽን አገልግሎቶች እንዲያገኙ ብሎም የተቀላጠፈ የጉምሩክ አሰራር እንዲኖር ማስቻል፡፡
- ምቹ የኢንቨስትመት ምህዳር እንዲፈጠር፣ ውጤታማ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስርዓቶች እንዲዘረጉና በአግባቡ እንዲተገበሩ በማድረግ በቱሪዝም ዘርፍ የውጭና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች እንዲስፋፉ ማድረግ፡፡
- የቱሪስት መዳረሻዎችን የሚያስተሳስሩ የትራስፖርት መሰረተ-ልማቶችን ማስፋፋት፤ የተሳለጠ የትራንስፖርት (የመንገድ፣ የአየር፣ የባቡር እና የውሃ) ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፡፡
- በዘርፉ ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ሀብት የማፍራት፣ የእውቀትና ክህሎት አቅርቦትና ፍላጎት እንዲጣጣሙ ማድረግ እንዲሁም የቱሪዝም ዘርፍ እድገት ማነቆዎችን ለይቶ ለመፍታት የሚያስችሉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማከናወን፡፡
- ዘመን አፈራሽ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተግባራዊ በማድረግ የቱሪዝም ዘርፉን በቴክኖሎጂ የማላቅ ስራ መደገፍ፤ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦች እንዲወጡ፣ እንዲዳብሩና ተግባራዊ እንዲደረጉ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ማበጀት፡፡
- በከተሞች የህዝብ አገልግሎት መስጫ ፋሲሊቲዎች (መጸዳጃ ቤቶችን፣ ማረፊያ ቦታዎችን፣ የከተማ ፓርኮች ወዘተ) እንዲስፋፉ፣ አስተማማኝ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲመቻች በማድረግ እና የቅርስ ጥበቃ ሥራን በመደገፍ የከተማ ቱሪዝም (Urban Tourism) እንዲጠናከር ማድረግ፡፡

- በአገር አቀፍ ደረጃ የሚቀረፁ ስትራጂዎችን መነሻ በማድረግ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችንና መሰል ሁነቶችን ወደ አገራችን በመሳብ የMICE ዘርፉን መደገፍ፡፡
- በተፈጥሮ አካባቢዎችና ባህላዊ ቅርሶች የሚገኙባቸው ስፍራዎች የሚካሄዱ የልማት ስራዎች ከቅርስ ጥበቃ እና ከቱሪዝም ልማት ስራዎች ጋር የተሳሰሩና የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
- በቱሪስት መዳረሻዎች የጤና ተቋማት እንዲስፋፉና የጤና የአገልግሎት እንዲሻሻል ማድረግ፤ የጤና ቱሪዝም (Medical tourism) እንዲጠናከር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዲሁም ከዘርፉ ተቋማት ጋር በትብብር ለቱሪስቶች የሚቀርቡ ምግቦችን ደህንነትና ንጽህና አጠባበቅ የመቆጣጠር ስራ ማከናወን፡፡
- በቱሪዝም እና በግብርና ዘርፎች መካከል ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ የግብርና ቱርዝም (Agro-Tourism) እንዲስፋፋ ማድረግ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥበቃ ስራ በተቀናጀ መልኩ እንዲጠናከር ማድረግ፤ የአረንጓዴ ቱሪዝም ልማት እንዲረጋገጥ መደገፍ፡፡
- ህገ-ወጥ የቅርስ ዝውውር እንዲሁም የዱር እንስሳት ዝውውርን የመከላከል ስራ ማገዝ፡፡
- በቱሪዝም መዳረሻዎች የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት እንዲሁም የውሃ እና ንፅህና (Sanitation) መሰረተ-ልማት እንዲስፋፋ ማድረግ፡፡
- የጎብኝዎች ደህንነት እንዲረጋገጥ ብሎም ለሚከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ ፍትህ የሚገኝበት አሰራር እንዲዘረጋ ማድረግ፡፡
- ከቱሪስት አመንጪ አገራት ጋር የአየር ትራንስፖርት ትስስር እንዲጠናከር ማድረግ፡ ፡
- በቱሪዝም መዳረሻዎች የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን መሰረተ ልማት እንዲስፋፋ በማድረግ የዲጂታላይዜሽን ስራዎችን ማገዝ፡፡
- በቱሪዝም ዘርፍ የአገልግሎት ጥራትን ከመሰረቱ ለማሻሻልና ልህቀትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶችን በንቃት መደገፍ፡፡
- የጉብኝት ባህል እንዲዳብርና ዜጎች ታሪካቸውን፣ ባህላቸውንና የተፈጥሮ ፀጋዎችን እንዲያውቁ ለማድረግ በሚካሄዱ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ንቅናቄዎችና ፕሮግራሞችን መደገፍ፤ በየተቋማት የጉብኝት ክበባት እንዲመሰረቱና ሰራተኞች አገራቸውን እንዲያውቁ ማበረታታት፡፡

### 7.1.2 የክልል አስፈፃሚ አካላት ሃላፊነቶች

- ከፖሊሲው የሚቀዱና በፌደራል ደረጃ የሚዘጋጁ የልማት ፕሮግራሞችና ስትራቴጂዎች ትግበራ ሂደት ግንባር ቀደም ተሳትፎ ማድረግ፣
- በፌዴራል ደረጃ ከሚቀረፁ የህግ ማዕቀፎች ጋር የተናበቡ ህጎችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የቱሪዝም ልማት ስራዎችን በብቃት ለመምራትና ለማስተዳደር እንዲቻል አደረጃጀቶችንና ተቋማዊ መዋቅሮችን ማጠናከር፣
- ፖሊሲውን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት አምዳዊና የጎንዮሽ የስራ ትስስሮችን በማጠናከር ስራዎችን በቅንጅት ማከናወን፣

- ከፌደራል አስፈፃሚ አካላት ጋር በመተባበር በነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እሴት በመጨመር እንዲሁም አዳዲስ መዳረሻዎችን በማልማት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣
- የቱሪስት መስህቦች እንዲለዩ፣ እንዲጠኑና በተሳሰረ መልኩ ለቱሪስቶች ምቹ ሆነው እንዲለሙ ድርሻን መወጣት፣
- በክልሉ በቱሪዝም ዘርፉ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ምቹ የኢንቨስትመንትን ምህዳር እንዲፈጠርላቸው መስራት፣
- በክልሉ በሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች የሰመረ የጉብኝት እንቅስቃሴ እንዲሰፍን ማስቻል፣
- ከመስህብ አካባቢ ማህበረሰቦች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በትብብር የቱሪዝም ሃብቶችን በተለይም ቅርሶችንና ጥበቃ ቦታዎችን መጠበቅና መንከባከብ፣
- በፌደራል ደረጃ የሚዘረጉ የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጥ፣ ደረጃ ምደባና ቁጥጥር አሰራር ስርዓቶችና ስታንዳርዶችን መሰረት በማድረግ በዘርፉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራት እንዲሻሻል ማድረግ፣
- ህጋዊ እውቅና የሌላቸውን የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማትንና ባለሙያዎችን መቆጣጠር፣
- ዜጎች አገራቸውን እንዲያውቁና የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲጠናከር ከፌደራል ተቋማት፣ ከግል ዘርፉ እና ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር መስራት፣
- በክልሉ ካሉ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሃይል ማፍራት፣ የሰው ሃይል አቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣
- ዘርፉን የተመለከቱ መረጃዎች በጥራት ማደራጀት፣ ማመንጨትና ማሰራጨት፣
- የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰቦች በቱሪዝም ልማት የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉና የጥቅሙ ተካፋይ እንዲሆኑ ማስቻል፣
- በክልሉ የቱሪዝም ዘርፍ የባለሙያዎችን ተሳትፎ እንዲጠናከር ማድረግ፣
- በክልሉ አነስተኛና መካከለኛ የቱሪዝም ንግድ ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣
- ከፌደራ መንግስት የቱሪዝም አስፈፃሚ አካል፣ ከግል ዘርፉና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን የቱሪዝም ፀጋዎችና መዳረሻዎች በልዩ ልዩ መንገድ የማስተዋወቅና የገፅታ ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣
- ከፌደራል የቱሪዝም ዘርፍ አስፈፃሚ አካል ጋር በመተባበር በክልሉ የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች ዘላቂነትንና ተወዳዳሪነትን ባማከለ ሁኔታ እንዲተዳደሩ አሰራር ስርዓችን መዘርጋት፣

### 7.1.3 የግል ዘርፍ ሃላፊነቶች

- የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማትንና ፋሲሊቲዎችን በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት በማቅረብ በቱሪዝም ልማት ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን፣
- አነስተኛ፣ መካከለኛ እነ ከፍተኛ አገልግሎት ሰጭ ተቋማንና ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም የዘርፉን ኢንቨስትመንት ማሳደግ እና የስራ እድሎችን ማስፋፋት፣
- ዘርፉን የሚያግዙ አዳዲስ የንግድ ሀሳቦችን በማመንጨት እና ተግባራዊ በማድረግ የፈጠራ (Entrepreneurship) ባህል እንዲጎለብትና እንዲሰርፅ ማድረግ፣

- የቱሪዝም ግብይትና ማስተዋወቅ ተግባራት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ በአገር ገፅታ ግንባታ ስራዎችን ውጤታማ አስተዋፅዖ ማድረግ፣
- በዘርፉ ብቁ የትምርትና ስልጠና ተቋማት እንዲፈጠሩ እና የሚያሰለጥኗቸው ባለሙያዎች በእውቀትና በክህሎት የተካኑ ሆነው እንዲወጡ ለማስቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር መስራት፣
- በቱሪዝም መስህቦችና መዳረሻዎች እንዲሁም በቱሪስት መስመሮች መሰረተ-ልማት የማስፋፋት ስራን መደገፍ፣
- ለቱሪስቶች ጥራት ያለውና ለሚከፈል ዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት መስጠት፣
- አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በሰለጠኑ ባለሙያዎች እንዲመራና እንዲደረጁ ማድረግ፣ በተቋማቱ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞችን አቅም መገንባታ፣
- ለአገር ውስጥ ቱሪዝም ልማት ትኩረት በመስጠት ዜጎች አገራቸውን እንዲያውቁና የጉብኝት ባህል እንዲዳብር አስተዋፅዖ ማድረግ፣
- የቱሪዝም ዘርፍ የስነ-ምግባር ደንቦችን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች በማክበር ጤናማ የንግድ ውድድር ባህልን እንዲሰፍን ማድረግ፣
- ዘላቂነትን የተከተሉ የአገልግሎት አሰጣጥና የንግድ አሰራሮችን በመተግበር ለዘላቂ ቱሪዝም ልማትን መጠናከር አስተዋፅዖ ማበርከት፣
- በታሪካዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ጥበቃ ስራ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣
- አደረጃጀቶችን/ማህበራትን በማጠናከር፣ በዓለም አቀፍ ቅንጅቶችና ጥምረቶች እንዲሁም የአጋርነት ማዕቀፎች ንቁ ተሳትፎ በማድረግ መብትና ጥቅሞቻቸውን ማስከበር፣

### 7.1.4 የሲቪል ማህበረሰብ አካላት ሚና

- በቱሪዝም መዳረሻ ልማትና አስተዳደር ስራዎች ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን፣
- የዘርፉን ችግሮች በጥናትና ምርምር መንቀስና የመፍትሄ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣
- ዘርፉን የሚያግዙ ስትራቴጂዎችና እቅዶች የመቅረፅ፣ ተግባራዊ የማድረግና የማሻሻል ሂደት ወስጥ ተሳትፎ ማድረግ፣
- በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የስልጠና እና አቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣
- ከአቻ ተቋማት ጋር ትብብር በመፍጠር ዘርፉን በተደረጃ መልኩ መደገፍ፣
- በሴክተሩ ለተሰማሩ ሌሎች አካላት የምክር፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የአድቮኬሲና የማስተባበር ስራዎችን ማከናወን፣
- እውቀት የሚጋራበት እና የሃሳብ ልውውጥ መድረኮች፣ ኮንፈረንሶች፣ ሴሚናሮችን ማዘጋጀት፣
- ዘርፉ በሰለጠኑ ባለሙያዎች እንዲንቀሳቀስ፣ በሳይንሳዊ መንገድ እንዲመራ እና የላቀ መረጃ አጠቃቀም ስርዓት እንዲኖር ድጋፍ ማድረግ፣
- ለዘርፉ ልማት ወሳኝ የሆነ ፋይናንስ ማፈላለግና ማመንጨት፣
- አዳዲስ አሰራሮችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ሃሳቦችን ማመንጨትና እንዲተገበሩ ድጋፍ ማድረግ፣ ጠቃሚ ልምዶችን መቀመር፣

### 7.1.5 የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰብ ሚና

- የቱሪዝም ሃብቶችን በባለቤትነት ስሜት በመጠበቅና በመንከባከብ እንዲሁም በመስህብ/መዳረሻ ልማትና አስተዳደር ስራዎች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ በማድረግ በአካባቢው የቱሪዝም ልማት ውስጥ ንቁ ተሳትፎን ማረጋገጥ፣
- የአካባቢ መስህቦችን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶችን በመልካም መንፈስ መቀበል፣ ተገቢውን እንክብካቤ መስጠት እና በአካባቢው የእንግዳ ተቀባይነት ባህል መሰረት ማስተናገድ፣ የአካቢውን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ፣
- በጎብኚዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረቱና የአካባቢውን ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች በጠበቀ መልኩ የቱሪዝም ምርትና አገልግሎቶችን ማቅረብ፣
- በአካባቢው የሚካሄዱ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች ከማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች ጋር የተስማሙ እንዲሁም የተፈጥሮ አካባቢን ሚዛን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ፤ የቱሪዝም አሉታዊ ተፅዕኖዎችን መከላከል፣
- በማህበረሰብ አቀፍ ቱሪዝም እንቅስቃዎችና ፕሮጀክቶች ተግበራ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ፣
- የኢኮቱሪዝም ልማት እንዲጠናከር ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በትብብር መስራት፣

## 7.2 የፖሊሲው ማስፈጸሚያ የሕግ ማዕቀፎች እና አሠራሮች

በጥናት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ይህንን ፖሊሲ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ አዳዲስ የህግ ማዕቀፎች ይዘጋጃሉ፤ ነባር የህግ ማዕቀፎችም እንዲሻሻሉ ይደረጋል፡፡

## 7.3. የቱሪዝም ፖሊሲውን ቁልፍ ውጤቶች ለማረጋገጥ የሚከናወኑ የልማት ፕሮግራሞች

**ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማሳደግ:-** የቱሪዝም ምርት ልማት ፕሮግራም፣ የቱሪዝም መሰረተ-ልማት ማስፋፋት ፕሮግራም፣ የኢንቨስትመንትና ኢንተርፕራይዝ ልማት ፕሮግራም፣ የመዳረሻ አስተዳደር ፕሮግራም፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም፣ የዓለም አቀፍ ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም፣ የኹነት ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም እና የስቶፕኦቨር ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የቱሪዝም ምርት ልማት ፕሮግራም የቱሪዝም ፀጋዎችንና የመልማት ዕድሎችን ለመለየት፣የቱሪዝም ምርቶችን ዓይነትና ብዛት እንዲሁም ጥራት ለማሳደግ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የቱሪዝም መሰረተ-ልማት ማስፋፋት ፕሮግራም የቱሪዝም መዳረሻዎች አስፈላጊ የሆኑ የመንገድና ትራንስፖርት፣ የመብራት፣ የውሃ፣ የቴሌኮም፣ የፋይናንስ ተቋማት እና የመሳሰሉት መሰረተ-ልማቶች እንዲሟሉ ለማድረግ ይከናወናል፡፡

የኢንቨስትመንትና ኢንተርፕራይዝ ልማት ፕሮግራም በዘርፉ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ምቹ እና ቀልጣፋ ለማድረግ እና የቱሪዝም ኢንተርፕራይዞችን ብዛት ለማሳደግ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የመዳረሻ አስተዳደር ፕሮግራም የቱሪዝም መዳረሻዎች በዘላቂነት እንዲለሙ፣ ተወዳዳሪነታቸው እንዲያድግ፣ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለው የልማት ትስስር እንዲጠናከር እና ከቱሪዝም የሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እንዲጨምር ለማድረግ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲያድግ እና ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለማህበራዊ አብሮነት፣ ለሰላም፣ ለጋራ መግባባት እና ለአገር ግንባታ

መሳሪያነት እንዲውል ለማስቻል ይከናወናል፡፡ የውጭ አገር ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም አገራችን ያሏትን መስህቦች እና የቱሪዝም ምርቶች በጠንካራ እና ፈጠራ በተሞላበት እንዲሁም በቴክኖሎጂ በታገዙ ልዩ ልዩ መንገዶች በማስተዋወቅ የውጭ አገር ጎብኝዎች ቁጥር እንዲያድግ፣ በመዳረሻዎች ፈሰስ የሚያደጉት ገንዝብ እንዲጨምር እና የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ከፍ እንዲል ለማስቻል ይከናወናል፡፡

የኹነት ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም አገራችን ያላትን ዕምቅ የኹነት ቱሪዝም ልማት ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል የኹነት መሰረተ-ልማቶችና ፋሲሊቲዎች እንዲስፋፉ እና ልዩ ልዩ ኹነቶች በአገራችን እንዲካሄዱ ለማስቻል ይተገበራል፡፡ የስቶፐኦቨር ቱሪዝም ልማት ፕሮግራም በቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ ትራንዚት መንገደኞች (Transit Passenger) አዲስ አበባን እንዲጎበኙ ለማስቻል የሚተገበር ፕሮግራም ነው፡፡

***ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና የተፈጥሮ ቅርሶችን የጥበቃና አጠቃቀም ሁኔታ ማሻሻል፡-*** *የታሪካዊ፣* ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ቅርሶች ጥበቃ እና አጠቃቅም ፕሮግራም፣ የተፈጥሮ ሃብቶች ጥበቃ እና አስተዳደር ፕሮግራም እና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡ የታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ቅርሶች ጥበቃ እና አጠቃቅም ፕሮግራም ቅርሶችን ማህበረሰቡን እና የቅርስ ባለቤት የሆኑ ሃይማኖት ተቋማትን ባሳተፈ መልኩ ለመለየት፣ ለመጠገን እና ለመጠበቅ፤ ለማህበረሰቡና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ስለቅርሶች ግንዛቤ ለመፍጠር፤ በቅርሶች ላይ የሚደርሱ ህገ-ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል እና በህገ-ወጥ መንገድ ከአገር የወጡ ቅርሶችን ለማስመለስ፤ በቅርሶች ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ እና ሌሎች ተጽዕኖዎችን ለመከላከል፤ ከቅርሶቹ የሚገኝ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያድግ እና በቅርሶች ላይ የሚካሄዱ የምርምር ሥራዎች እንዲጎለብቱ ለማድረግ የሚተገበር ፕሮግራም ነው፡፡

የተፈጥሮ ሃብቶች ጥበቃ እና አስተዳደር ፕሮግራም የጥብቅ ስፍራዎች ሽፋን እንዲያድግ፣ የተጎዱ ቦታዎች እንዲያገግሙ፣ የብዝሃ-ሕይወት መመናመን እንዲቀንስ፣ አደጋ ውስጥ ያሉ ብርቅዬ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት ቁጥር እንዲጨምር፣ የስነ ምድር ሃብቶች እንዲጠበቁ፣ በተፈጥሮ ሃብቶች ላይ የሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎችን ለመከላከል እና ለመቀነስ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ በቅርስ ጥበቃ እና ልማት ያለው ሚና እንዲጨምር ለማድረግ የሚከናወን ፕሮግራም ነው፡፡

ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ፕሮግራም የተፈጥሮ ሀብቶች ዘለቄታዊ አጠቃቀም ግንዛቤ ለማሳደግ፣ የተፈጥሮ የቱሪዝም ሀብቶች ልማት ከሌሎች የልማት ዘርፎች ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ለማስቻል፣ የልማት ስራዎች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢ፣ የቅርስ እና የማህበራዊ የተፅዕኖ ግምገማዎች እንዲደረጉ እና የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቅም ጥናትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ለማድረግ ይከናወናል፡፡

***ብቁ እና ተወዳዳሪ የሰው ሃይል እና ጠንካራ ተቋማዊ አቅምን ለመፍጠር፡-*** *የዘርፉ የሰው* ሀብት ልማት ፕሮግራም፣ ተቋማዊ አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ የቱሪዝም መረጃ እና ምርምር እንዲሁም ስርጸት ማሻሻያ ፕሮግራም የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ የሰው ሀብት ልማት ፕሮግራም የመንግስት፣ የግል እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት አመራሮችን እና ባለሙያዎችን አቅም ለመገንባት፣ ተግባር-ተኮር የሆነ ስልጠናና ትምህርት ለመስጠት፣ የተመረጡ የአመራርነት ሙያዎች ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲመሩ ለማድረግ የሚተገበር ይሆናል፡፡ ተቋማዊ

አቅም ግንባታ ፕሮግራም በመንግስት የቱሪዝም ተቋማት መካከል የሚስተዋለውን የመዋቅር አለመናበብ ለማስተካከል፣ የዘርፉ ተዋናዮች የሚሳተፉባቸውና ለጋራ ዓላማ የሚመካከሩባቸው መድረኮችን ለማመቻቸት፣ የዘርፉን የፋይናንስ ውስንነት ለመቅረፍ እና ድንገተኛ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስችል አቅም ለመገንባት የሚተገበር ይሆናል፡፡

የቱሪዝም መረጃ እና ምርምር እንዲሁም ስርጸት ማሻሻያ ፕሮግራም በዘርፉ የሚስተዋለውን የመረጃ አያያዝ እና ጥራት ችግር ለማሻሻል፣ የቱሪዝም ሳተላይ አካውንት ሥራን ለማጠናከር፣ በዘርፉ የሚካሄደውን የምርምር ስራዎች ለማሳደግ፣ የሃሳብ ማበልጸጊያ እና የፈጠራ ማዕከላትን ለመመስረት እና የመረጃ እና ምርምር ስራዎችን ስርጸት ለማሳደግ የሚተገበር ይሆናል፡፡

**የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ትብብርና አጋርነትን ለማሳደግ**:- ባለብዙ ወገን የቱሪዝም አስተዳደር ፕሮግራም እና ቀጠናዊ የቱሪዝም ልማት ትስስር ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ ባለብዙ ወገን የቱሪዝም አስተዳደር ፕሮግራም የዘርፉ ተዋናዮች ተሳትፎ እና ትብብር ለማሳደግ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እና የተለያየ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ለማስቻል የሚተገበር ይሆናል፡፡ ከጎረቤት አገሮች ጋር ያለውን የቱሪዝም ልማት ትስስር ለማጠናከር እና ከዓለም አቀፍ አጋር አካላት ጋር ያለውን ትብብር ለማሳደግ ቀጠናዊ የቱሪዝም ልማት ትስስር ፕሮግራም የሚተገበር ይሆናል፡፡

**የአገልግሎት ልህቀትን ለማረጋገጥ**:- የአገልግሎት ጥራት አስተዳደር ፕሮግራም እና የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን የማብቃት ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የአገልግሎት ጥራት አስተዳደር ፕሮግራም ህጋዊ እውቅና ያገኙ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ሽፋን/ቁጥር ለማሳደግ፣ የደረጃ ምደባ ስራን ለማጠናከር፣ ለአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ማሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ ደረጃ ለማዘጋጀት እና የአገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚተገበር ይሆናል፡፡ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን የማብቃት ፕሮግራም በዘርፉ የሚስተዋለውን የአግልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የማማከር፣ ቴክኖሎጅ እና ዘመናዊ አሰራርን እንዲጠቀሙ የማበረታታት እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለመስራት የሚተገበር ፕሮግራም ነው፡፡

### 7.4 የፖሊሲውን ውጤታማ አፈፃፀም የሚያረጋግጥ የክትትልና ግምገማ ስርዓት

የፖሊሲ ትግበራው የሚጠበቁትን ቁልፍ ውጤቶች ማምጣቱን በማረጋገጥ የማይበገር፣ ተወዳዳሪና ዘላቂ የቱሪዝም ዘርፍ ለመገንባት የክትትልና ግምገማ ስራ ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡ የክትትልና ግምገማ ስራው የሚያስፈልገው የፖሊሲውን ቁልፍ የውጤት መስኮችን ለማሳካት የሚጠቅሙ የቱሪዝም ልማት ፕሮግራሞች አፈጻጸም ላይ ነው፡፡

ይህ ሥራ የፖሊሲውን ቁልፍ ውጤቶች ለማሳካት፣ ክፍተቶች ሲኖሩ በወቅቱ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እና ፖሊሲውን ለመከለስ በቂ ምክንያት መኖር አለመኖሩን ለመረዳት ይጠቅማል፡፡ ስለዚህ የሚከተሉት የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. በፖሊሲው የልማት ፕሮግራሞች መሰረት የአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ጊዜ ዕቅዶች ይዘጋጃሉ፤ አፈጻጸማቸው በሚኒስቴሩ እና ተጠሪ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች ክትትልና ግምገማ ይደረግባቸዋል፡፡

2. የፖሊሲ የትግበራ ዕቅድ፣ ትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ስራን የሚሰራ ራሱን የቻለ የፖሊሲ ትግበራ የስራ ክፍል በሚኒስቴሩ ስር ይቋቋማል። ከዚህ በተጨማሪ የቱሪዝም ካውንስል አንዱ ስራው የፖሊሲውን አፈጻጸም መከታተል ይሆናል።
3. የቱሪዝም ልማት ፕሮግራሞችን ተግባራዊነት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚረዳ ዲጂታል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ይዘጋጃል፤ በተገኘው ግብዓት መሰረት ጊዜውን የጠበቀ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል።
4. የቱሪዝም ልማት ፕሮግራሞች በፖሊሲ ትግበራ ዕቅዱ መሰረት በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች በትክክል እየተተገበሩ መሆኑን ለማረጋገጥ የክትትል ስራዎች በየጊዜው ይሰራሉ።
5. የፖሊሲው ቁልፍ የውጤት መስኮች አፈጻጸም በየሶስት ዓመቱ ይገመገማል፤ የግምገማ ውጤቶቹ ቀጣይ ስራዎችን ለማሻሻል በግብዓትነት እንዲያገለግሉ ይደረጋል። ፖሊሲው ያመጣውን ውጤት ሳይንሳዊ በሆነ እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ እንዲጠና ይደረጋል።
6. ፖሊሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፖሊሲ ፋይዳ ጥናት ላይ ተመስርቶ እና የአገርና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሻሻል ይደረጋል።

## 8. ሌሎች ተዛማጅ የልማት ፖሊሲዎች

የቱሪዝም ፖሊሲ ጉዳዮችንና ስልታዊ አቅጣጫዎችን ለመተግበር የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ የልማት ፖሊሲዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 8.1 የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች እና መሰረተ-ልማት ፖሊሲዎች

የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ጥራት ያላቸውን የግብርና ምርቶች ማምረት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እና በቀጣይነት ለቱሪዝም የንግድ ተቋማት ወይም ቢዝነሶች እንዲያቀርብ ይጠበቃል። ይህም በቱሪዝምና ግብርና መካከል ያለውን ትስስር በማሳደግ የኢኮኖሚ ዕድገትን ያመጣል። ከዚህ በተጨማሪ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ የገጠር ልማት እና የገጠር ቱሪዝምን (Rural tourism) ማስተሳሰር መቻል አለበት። የማዕድን ፖሊሲ የጂኦሄሪቴጅ ሀብቶችን በዘላቂነት መጠቀምና ከቱሪዝም (በተለይ ከጂኦቱሪዝም) ጋር ማስተሳሰር ይጠበቅበታል። የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ፖሊሲ ለቱሪዝም የንግድ ተቋማት ወይም ቢዝነሶች ቀልጣፋ በሆነ መልኩ የንግድ ፈቃድ መስጠት እንዲሁም የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት ለቱሪዝም የንግድ ተቋማት ምቹ የስራ ሁኔታ እንዲፈጥር ይጠበቃል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ፖሊሲ የቱሪዝም ትራንስፖርትን ማስፋፋት እና እንከን የለሽ የትራንስፖርት ትስስር (ለምሳሌ የየብስ፣ አየር፣ ባቡርና ውሃ) በአገር ውስጥ እንዲፈጠሩ ማድረግ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ ፖሊሲው ጎብኝዎች ከሚመጡባቸው አገራት ጋር የአየር ትራንስፖርት ትስስር መፍጠርና ትስስሮችን ማጠናከር ይጠበቅበታል። የኢነርጂ ፖሊሲ ለቱሪዝም መዳረሻዎችና ቢዝነሶች አስፈላጊውን የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲያቀርብ ይጠበቃል። የውሃ ፖሊሲ የቱሪዝም መዳረሻዎች የመጠጥ ውሃ እና የሳኒቴሽን መሰረተ-ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል።

### 8.2 የማህበራዊ እና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲዎች

የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተግባር ተኮር ስልጠናና ትምህርት በመስጠት ለቱሪዝም ዘርፍ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሀብት ያመርታል፣ ያቀርባል። ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎችን በመስራትና በማሰራጨት የዘርፉን የልማት ማነቆዎች ይፈታል፣ የዘርፉን አቅም ይገነባል። የጤና ፖሊሲ በምግብ ደህንነትና ንጽህና፣ ለቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማትን ጥራት እንዲሁም የህክምና እና የጤና ቱሪዝምን (Medical and Wellness Tourism) በማበረታታት ዙሪያ ስራዎችን ይሰራል። የባህል ቅርሶችን የመለየት፣ የመጠበቅ እና የማልማት ስራ ከባህል ፖሊሲ ይጠበቃል።

### 8.3 የሳይንስ፣ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ በቱሪዝም ዘርፍ የዲጅታላይዜሽንና ኢኖቬሽን ስራዎችን የማስተዋወቅ እና ለቱሪዝም ቦታዎች አስፈላጊ ካርታዎችን ማዘጋጀት፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በቴክሎጂ ማጠናከር፣ የቱሪዝም እሴት ሰንሰለትን ማዘመን ይጠበቅበታል።

### 8.4 የፍትህና አስተዳደር ፖሊሲዎች

የመንግሥት የአገልግሎትና አስተዳደር ፖሊሲ ለመንግስት የቱሪዝም ተቋማት አስፈላጊውን ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር እና ለሰራተኞች የማበረታቻ አሰራሮችን ወይም ፓኬጆችን መቅረጽ ይጠበቅበታል።

## 9. መሰረታዊ የቃላት ፍቺ

**ቱሪዝም** ማለት ጎብኝዎች በተናጠል ወይም በቡድን በመሆን በቋሚነት ከሚኖሩበት አካባቢያቸው የዕረፍት ጊዜን ለማሳለፍ፣ ለመዝናናት ዘመድ እና ጓደኛ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ለጥናትና ምርመር፣ ለሃይማኖታዊ ጉዳይ፣ ኹነቶች ላይ ለመሳተፍ፣ እና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ አገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሱበት ቦታ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ ሲቆዩ የሚፈጠር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስተት ነው።

**ጎብኝ** ማለት አንድ ሰው በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢው ለመዝናናት፣ ዘመድ እና ጓደኛ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ለጥናትና ምርመር፣ ለሃይማኖታዊ ጉዳይ፣ ኩነቶች ላይ ለመሳተፍ፣ እና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ አገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሰበት ቦታ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ሰው ነው።

**የአገር ውስጥ ጎብኝ** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር አንድ ሰው በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢው ለመዝናናት፣ ዘመድ እና ጓደኛ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ለጥናትና ምርመር፣ ለሃይማኖታዊ ጉዳይ፣ ኩነቶች ላይ ለመሳተፍ፣ እና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ አገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሰበት ቦታ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ሰው ነው።

**የውጭ አገር ጎብኝ** ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖር አንድ ሰው በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢው ለመዝናናት፣ ዘመድ እና ጓደኛ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ለጥናትና ምርመር፣ ለሃይማኖታዊ ጉዳይ፣ ኩነቶች ላይ ለመሳተፍ፣ እና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ አገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሰበት ቦታ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ሰው ነው።

**የጎብኝዎች አገልግሎት ሰጭ ተቋማት** ማለት ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣ ሞቴሎች፣ እንግዳ ማረፊያዎች፣ አስጎብኝ ድርጅቶች፣ ግለሰብ አስጎብኝዎች፣ የቱሪዝም ትራንስፖርት

አቅራቢዎች እና ሌሎች በቱሪዝም እሴት ሰንሰለት ውስጥ ተሰማርተው ለጎብኝዎች አገልግሎት የሚያቀርቡ የንግድ ተቋማት ናቸው።

**አስጎብኝ ድርጅት** ማለት ልዩ ልዩ የጉዞ ፕሮግራሞችንና የጉብኝት ፓኬጆችን በመንደፍና በማቀናጀት እና በማስተዋወቅ ለውጭ እና ለአገር ውስጥ ቱሪስቶች የሚሸጡ ድርጅች ናቸው።

**ግለሰብ አስጎብኝ** ማለት ለጎብኝዎች ስለ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሮአዊ የቱሪዝም መዳረሻዎች ጥልቅ እውቀት እና ትርጓሜ የሚሰጥ ባለሙያ ግለሰብ ማለት ነው።

**የቱሪዝም ግብይት** ማለት የዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ጎብኝዎችን ፍላጎት በማጥናት የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ የጎብኝ መዳረሻዎች፣ የቱሪዝም ምርቶችና አገልግሎቶች የሚመለከቱ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን በማስተዋወቅና የሽያጭ ስራዎችን በማከናወን አገሪቱ ከቱሪዝም ዘርፍ የምታገኘውን ጠቀሜታ ለማሳደግ የሚከናወን ስራ ነው።

**ታሪካዊ እና ባህላዊ ቅርስ** ማለት ማንኛውም የሚዳሰስም ይሁን የማይዳሰስ በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት የሆነ የሰውን ልጅ ዕድገት የሚያሳይ እና ሳይንሳዊ፣ ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ኪነ-ጥበባዊ እና ዕደ-ጥበባዊ እሴት ያለው ነው።

**የተፈጥሯዊ ቅርስ** ማለት የጎብኝዎችን ቀልብ መሳብ የሚችሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት፣ ማራኪ መልክዓ-ምድርን እንዲሁም የጂኦሎጂ ውጤቶችን የያዘ ነው።

**ጥበቃ** (Conservation) ማለት የተፈጥሮ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን እንክብካቤ፣ ጥገና፣ መልሶ መገንባት፣ ከጉዳት መከላከልን እና ባለበት እንዲቀጥል ማደረግን ያካትታል።

**ሙዚየም** ማለት ባህላዊ እና/ወይም የተፈጥሮ ቅርሶችን የሚሰበስብ፣ የሚጠብቅ እና የሚጠግን ብሎም ለምርምር፣ ጥናት፣ ትምህርት እና መዝናኛ የሚጠቅሙ ስብስቦችን በማዘጋጀት እና በማደራጀት፣ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ማለት ነው።

**የኹነት/ማይስ ቱሪዝም** - 'MICE Tourism' ማለት ስብሰባዎችን፣ የማበረታቻ ጉዞዎችን፣ ኮንፈረንሶችን እና ኤግዚቢሽኖችን (Meetings, Incentives, Conferences, and Exhibitions) መሰረት ያደረገ የቱሪዝም ዓይነት ነው።

**ጂኦሄሪቴጅ** ማለት ባላቸው እሴት ወይም ጠቀሜታ ምክንያት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን የጂኦሎጂ እና የመልክዓ-ምድር ቅርሶች/መስህቦችን የያዘ ነው።

**ጂኦቱሪዝም** ማለት ጂኦሄሪቴጅን ወይም የጂኦሎጂ እና የመልክዓ-ምድር መስህቦችን መሰረት ያደረገ የቱሪዝም ዓይነት ነው።

**ጂኦፓርክ** ማለት በውስጡ አገር አቀፍ/ዓለም አቀፍ የሥነ-ምድር (ጂኦሎጂካል) እሴት ያላቸውን ቅርሶች የያዘ ጥብቅ ቦታ ነው። ከሥነ-ምድር ቅርሶች በተጨማሪ በውስጡ ሌሎች የተፈጥሮ፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ ቅርሶችን ሊይዝ ይችላል።

**ስቶፐኦቨር ቱሪዝም** ማለት በቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ውስጥ ረዘም ያለ ጊዜ ያላቸው ተላላፊ (Transit Passengers) መንገደኞች አዲስ አበባንና ሌሎች የጎብኝ መስህቦችን እንዲጎበኙ የሚደረግበት የቱሪዝም ዓይነት ነው።

**የቱሪዝም ምርት** ማለት የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ሀብቶች፣ አገልግሎቶችን እና እንቅስቃሴዎችን የሚያጠቃልል እና ዋጋ ወጥቶለት ለጎብኝዎች የሚሸጥ ነው::

**ባለብዙ አማራጭ የትራንስፖርት ሥርዓት** /Multi-modal transport system/ ማለት ጎብኝዎች የተሳሰረ፣ የተሳለጠ እና ብዙ አማራጭ ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ሥርዓት ነው::

**የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዞን** ማለት ለቱሪዝም ዘርፍ ኢንቨስትመንት እና ልማት የሚሆን በጥናት የተለየ ቦታ ማለት ነው::

**ስማርት የቱሪዝም መዳረሻ** ማለት ጊዜውን በዋጀ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የተደራጀ እና የጎብኝዎችን እርካታ የተሻለ የሚያደርግ የቱሪዝም መዳረሻ ማለት ነው::

**የመዳረሻ ልማት** ማለት በመዳረሻው የሚገኙ የቱሪዝም ሃብቶች ላይ እሴት መጨመር የቱሪዝም ምርቶችን ማልማት፣ መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት፣ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ማስፋፋትና አገልግሎታቸውን ማሻሻል፣ ቅርሶችን መንከባከብ፣ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል::

**የመዳረሻ አስተዳደር** የጎብኝዎችን፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ እና የቱሪዝም ቢዝነሶችን ፍላጎት እና ተጠቃሚነት ከግምት ውስጥ ያስገባ ሁሉን አቀፍ የሆነ የመዳረሻ ዕቅድ፣ ልማት እና አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት መዳረሻዎች በዘላቂነት የሚተዳደሩበት ሥርዓት ነው::

**ዘላቂ ቱሪዝም** ማለት የአሁንና የወደፊት ኢኮኖሚያ፣ በባህል እና አካባቢያዊ ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ያስገባ እና የጎብኝዎችን፣ የማህበረሰቡን እና የዘርፉን ባለድርሻ አካላት ፍላጎት የሚያሟላ የቱሪዝም ዓይነት ነው::

**ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃ** ማለት አንድ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ለደንበኞቹ ሊሰጠው የሚገባውን ዝቅተኛ የምርት እና አገልግሎት ጥራት ሁኔታን የሚገልጽ ስታንዳርድ ነው::

**ብቃት ማረጋገጥ** በቱሪዝም ዘርፍ የሚሰማሩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት ማሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች በማረጋገጥ መስራት እንደሚችሉ ህጋዊ እውቅና የሚሰጥበት ሥርዓት ነው::

**የተመጣጠነ ዋጋ** /Value-for-money/ ማለት ደንበኞች ለገዙት ምርት እና ላገኙት አገልግሎት የሚመጥን ክፍያ ማለት ነው::

**ድንበር ተሻጋሪ የቱሪዝም ሀብት** ማለት በኢትዮጵያ እና ጎረቤት አገራት (መካከል) የሚገኝ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና የተፈጥሮ ቅርሶችን የሚመለከት ነው::

**ባለድርሻ አካል** ማለት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ በቀጥታ ተጽዕኖ ያለው ወይም ደግሞ በቱሪዝም ዘርፉ ተጽዕኖ የሚደርስበት አካል ነው::

**የፆታ አገላለፅ**: በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ የሴትንም ፆታ ያካትታል::